ጻድቁ አባታችን

አቡነ
እስትንፋሰ ክርስቶስ

የማክሰኞ

አክብር፣ ዘመንህ እንዲበዛልህ እናትህንና አባትህን አክብር፣ አትግደል፣ አትስረን፣ አትሥረቅ፣ በወንድምህ ላይ በሐሰት አትመስክር፣ የወንድምህን ገንዘብ አትመኝ፣ ወንድምህን እንደራስህ ውደድ የሚለውን ይህንን ቃል ለእስትንፋስ ክርስቶስ በሚነገርበት ሰዓት (ጊዜ) መነኮሳት የሚያስፈራ ድምፅና የነጋሪት ድምፅ ይሰሙ ነበር::

፲፱ ታላቅ ብርሃንም ያዩ ነበር፣ ተራራውም ይጤስ ነበር፣ ህዝብና መነኮሳት ሁሉ ፈርተው ከሩቅ ሆነው ይመለከቱ ነበር፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን ቀድሞ ለአንድ ወጣት እንደነገረው ዳግመኛ እንደዚሁ ለአባታችን እስትንፋስ ክርስቶስ አትግደል፣ ወደ ሌላ ሰው ሚስት አትሂድ፣ አትሥረቅ፣ በሐሰት ምስክር አትሁን፣ እናትህንና አባትህን አክብር፣ ወንድምህን እንደራስህ ውደድ፣ ብሎ ሰጠው:: ጸሎቱና በረከቱከአካለ ወልድና ከወለተ ሰማዕት ጋር ይሁን ለዘለዓለሙ፣

ምዕራፍ ፫ : የሩቡዕ::

ይህንን ከሰጠው በኋላ ሰውን ሁሉ አስተምርልኝ፣ ይህንን ያልጠበቀ ወደ መንግሥተ ሰማያት አይገባም አለው፣ ከዚህ በኋላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለብፁዕ አባታችን እስትንፋስ ክርስቶስ ስለወደድከኝ ፈቃዴን ስለፈጸምክ ስለ ብዙ ድካምህና መከራህ ለኔ ስለተጋደልክ፣ እኔም በአንዲት ቀን አሥር ሺህ አሥር ሺህ ነፍሳትን እምርልሃለሁ፣ በሶስቱ በዓላት በተወለድኩበት፣ በተጠመቅሁበት፣ በተነሳሁበት እንደዚሁ ሰባ ሺህ ሰባ ሺህ ነፍሳትን በቀን ሰባት ጊዜ በሌሊት ሰባት ጊዜ እስከ ዕለተ ምፅአት ድረስ እምርልህለሁ አለው::

ዳግመኛም ዝክርህን የዘከረ፣ ስምህን የጠራ፣ የገድልህን መጽሐፍ የጻፈ፣ ያጻፈ፣ ያነበበ፣ የሰማ፣ የተረጎመውን እምርልሃለሁ አለው::

CamScanner

የረቡዕ

አባታችን አቡነ አስትንፋሰ ክርስቶስ ጌታችንን ልደትህ ስንት ነው? ሁለት ነው የሚሉ አሉ፣ ሦስትም ነው የሚሉ አሉ፣ እስኪ ንገረኝ አለው፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ከእግዚአብሔር አብ ያለ እናት ተወለድኩ፣ ድህረ ዓለም ከድንግል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቼ ሥጋና መለኮትን አዋህጄ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ በመሆን ተወለድኩ::

ወዳጄ አስትንፋሰ ክርስቶስ ሆይ እራሱ ክቡር፣ እራሱ አክባሪ፣ እራሱ የሚያከብር ነው በል፣ ሀሰተኞች መናፍቃን የጸጋ ልጅ ይሉኛል፣ ስለዚህ እነሱን አልወዳቸውም፣ በእነርሱም ላይ የሚገዟቸውን እና የሚያጠፏቸውን ጨካኞች አህዛብን አስለጥንባቸዋለሁ::

ዳግመኛም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የበህርይ ልጁ፣ የምዕመናን በኩር ሊቀ ካህናት የነገሥታት ንጉሥ፣ ዓለማትን የሚገዛ፣ ሕይወትን የሚሰጥ እንደ ነፍስና ሥጋ ተስብዕት ከመለኮት መለኮት ከትስብዕት በተዋህዶ ከበረ በል:: መጽሐፍ ቃል ሥጋ ሆነ ያም ቃል እግዚአብሔር ነው እንዳለ:: ዮሐ ፩፡፩

ለአባታችን ለአቡነ አስትንፋሰ ክርስቶስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ከነገረው በኋላ የስሜ ትርጓሜ አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ማለት ነው፣ ኢየሱስ ማለት የዓለም መድኃኒት ማለት ነው፣ ክርስቶስ ማለት የከበረ፣ ክቡር፣ የሚያከብር ማለት ነው:: ማሰያስ ማለት መሲህ የእግዚአብሔር አብ የባህርይ ልጅ መሲህም ማለት ለመንግሥትና ለክህነት በድንግል ማርያም ማህፀን በተዋህዶ የከበርኩ በመለኮቴ ሁሉን ሰጪ ስሆን፣ በሰውነቴ በተዋህዶ ከበርኩ::

ስለዚህ ነቢዩ ዳዊት በተዋህዶ ከበረ እንዳለ ሁለት ልደት ነው፣ ወልደአብ ወልደ ማርያም የሚል በእኔ ፊት እና በአባቴ ፊት የተፈታ ንፁህ ይሁን (ይሆናል) የእሳት ባህር አይነካውም በግልጥ ከአንተ ጋራ ያልፋል፣ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ያለ እናት ከአብ ተወለድኩ፣ ዓለም ከተፈጠረ በኋላ ያለአባት ከድንግል ማርያም ተወለድኩ፣ በምድር አባት የለኝም በሰማይም እናት የለኝም:: ወዳጄ አስትንፋሰ ክርስቶስ ሆይ ትክክለኛ ሃይማኖት ተዋህዶ ናት::

CamScanner

የረቡዕ

ዳግመኛም ሦስት ልደት ነው የሚል በእኔ ሥልጣን እና በአንተ ሥልጣን የተወገዘ፣ የተለየ ይሁን። በአፍአ የመንፈስ ቅዱስ ልጅ ነው የሚሉኝ ከአምስት ውሸች ጋራ በዕለተ ምፅአት ከመንግሥተ ሰማያት ይወጣሉ። ሁለቱን ልደቴን የሚክዱ ወየውላቸው፣ ወዮታ አለባቸው፣ ያን ጊዜ በመጨረሻ ቀን በዕለተ ምፅአት የከፋ ፍርድን እፈርድባቸዋለሁ። ሁለት አባት ሁለት እናት አለው የሚል የተወገዘ የተለየ ይሁን፣ ያለ ፈቃዱ ሞተ የሚል የተለየ የተወገዘ ይሁን። በለውነቱ (በመለኮቱ) ፍጡር ነው የሚል በእኔ ቃል እና በአንተ ቃል የተለየ የተወገዘ ይሁን። በለውነቱ (በመለኮቱ) ፍጡር ነው የሚል በእኔ ቃልና እኔ ለአንተ በለጠሁም በአንተም ቃል የተለየ፣ የተወገዘ ይሁን።

ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና ሃይማኖትን ከአቀኑ ከሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት ሃይማኖት ያጎደለ ሦስት ልደት ነው ብሎ የጨመረ በእነርሱ ቃል የተለየ፣ የተወገዘ ይሁን፣ ሐዋርያትና ሃይማኖታቸው የቀና ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት ከአስተማሩት ውጪ ሌላ ሃይማኖት የሚያስተምር ቢኖር የተወገዘ፣ የተለየ ይሁን። የጸጋ ልጅ ነው የሚል የተወገዘ ነው። አስቀድሞ ኢያኔስና ኢያንበሬስ በሙሴ ላይ ቢፀሀላውያን በሐዋርያት ላይ በጠላትነት እንደተነሱ መናፍቃን አርዮስና መቅዶንዮስ፣ ንስጥሮስም እንደ ተነሱ እንደዚሁ በመጨረሻ ዘመን መናፍቃን በኢትዮጵያ አገር ይነሳሉ፣ ብዙ ጸብንና ክርክርን ያነሳሉ፣ እሾህና አሜከላን ይተክላሉ፣ በስንዴም መካከል እንክርዳድን ይዘራሉ። ማቴ ፲፫፥፳፭ ፣

ዳግመኛም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእኔ አፍና በአባቴ አፍ፣ የባህርይ ህይወቴ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አፍ፣ በእናቴ በድንግል ማርያም አፍ በአሥራ አምስቱ ነቢያት አፍ፣ በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አፍ በሰባ ሁለቱ አርድዕት አፍ ሃይማኖታቸው በቀና አርዮስን ለማውገዝ በኒቅያ በተሰበሰቡ በሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት አፍ መቅዶንዮስን ለማውገዝ በቁስጥንጥንያ በተሰበሰቡ በመቶ ሃምሳ ሊቃውንት አፍ ንስጥሮስን ለማውገዝ በኤፌሶን በተሰበሰቡ በሁለት መቶ ሊቃውንት አፍ ልጄ እስትንፋስ ክርስቶስ ሆይ በአንተም አፍ የተለዩ፣ የተወገዙ፣ የታሰሩ ይሁኑ። ማቴ ፲፮፥፲፱

የሬቡዕ

፲፩ በሃይማኖት መናፍቃንን የሚከተል የተወገዘ ይሁን፣ ያለንሰሐ ለበደለኞች መጽደቅ ይቻላል የሚል የተወገዘ ይሁን፣ ሌላ ሕግ፣ ሌላ ሃይማኖት ይመጣል የሚል የተወገዘ ይሁን፣ አሪት በወንጌል አለፈች ነቢያት በሐዋርያት አለፉ የሚል የተወገዘ ነው። በቤተ ክርስቲያን ፀብ ክርክርን የሚያደርግ የተወገዘ ነው። ሐዋርያት ሃይማኖትን ያቀኑ ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት አጠፉ፣ ከእነሱ ይልቅ እኔ አሳምራለሁ የሚል የተወገዘ ይሁን።

፲፪ በቀኖናቸው ድድስቅልያ በተባለ መጽሐፋቸው እና የሐዋርያት ሥራ በሚባል መጽሐፋቸው ወይም በመልክታቸው መጽሐፍ (የሚሳሕቁ) በእነሱ አፍ የተወገዘ፣ የተለየ፣ የታሰረ ነው። ሥላሴ በአካል ሦስት አይደሉም ሁለት ወይም ሦስት አይደሉም አራት ናቸው የሚል፣ በአንድነታቸው ምንታዌ በሦስትነታቸው ርባኤ አለ የሚል የተወገዘ ይሁን አለው።

፲፫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአባታችን ከአቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ ጋር መነገር ከፊፀመ በኋላ አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስም እኔና ቤተሰቦቼ ሥላሴ አንድ ሲሆኑ ሦስት ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸው በማለት አንድም ሦስትም ብለን እናምናለን፡አለ።

፲፬ ዳግመኛም አባታችን የክርስቲያን ዕድል ፈንታቸው ጽዋ ተሮታቸው አንዲት ሃይማኖት እሷም ተዋህዶ ናት፣ አንዲት ጥምቀት የሃይማኖት ፍሬና የራሴ ዘውድ ይህች ሃይማኖት ተዋህዶ ናት። መጽሐፍ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት እንዳለ፣ ኤፌ ፬፡፬ ፡አለ።

፲፭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መልሶ አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስን ከአረመኔዎችና ከመናፍቃን ነገሥታትና ከመኳንንት የተነሳ አትፍራ፣ እኔ የሰማይና የምድርን ስልጣን አፍና ጥበብን፣ ንጽህናንና ትዕግስትን፣ ፍቅርንና የዋህነትን ተስፋንና ፈጽሞ ማመስገንን ሰጠሁህያለማንደል ሁሉን ትመልስላቸው ዘንድ እንደምትችል አድርጌህ ለሁ አለው።

የረቡዕ

፲፮ ይህን ብሎ ከአፀና በኋላ ሚካኤልና ገብርኤል፣ ሱራፌልና ኪሩቤል ኡራኤልና ሩፋኤል ሱሪያልና ፋኑኤል አፍኒንና ራጉኤል፣ ሳቁኤልም ተከትለው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ልዩ ክቡር ንጹህ አቸናፊ እግዚአብሔር ጌትነትህ በሰማይና በምድር የሞላ ነው፣ እያሉ በክብር ወደ ሰማይ አረገ፣ ይህን እያሉ እስከ ፯ኛ ሰማይ አደረሱት::

፲፯ አባታችን እስትንፋስ ክርስቶስም ከነሱ ጋራ ነበር፣ በዝያም ቦታ ነብያትና ሐዋርያት ጻድቃንና ሰማዕታትን አየ ጌታችንም ሚካኤልና ገብርኤልን ጠባቂ አድርጎ ሰጠው ይህንን የነገርኩህን ሃይማኖት ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ የኢትዮጵያን አውራጃ ሁሉ አስተምርልኝ::

፲፰ ነገር ግን ከኔ ጋራ ወደ ሰማይ ማረግህን ውዳሴ ከንቱ እንዳይሆንብህ ለማንም አትግለጥ፣ ወልደ አብ፣ ወልደ ማርያም በተዋህዶ ከበረ ብለህ ሁለት ልደቴን አስተምር እንጅ አለው:: ከዚህ በኋላ ደስታና ኃይልን ሞልቶ ጌታችን ቃልኪዳን ሰጥቶት አባታችንም ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋራ ወደ ባዕቱ ተመለሰ፣ በባዕቱም ውስጥ እጅግ ጸለየ:: ማቴ ፮፥፮

፲፱ ከዚህ በኋላ አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋር ተነስቶ እየጸለየ ከአስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋር ሔዶ ወደ ሸዋ ምድር ደረሰ ያገሩም ሰዎች በክብር ተቀበሉት::

ምዕራፍ ፮

፩ በዚያም የወንጌል ትምህርት አስተማረ በዚያም ብዙ አድባራትንና አብያተ ክርስትያናትን አሳነፀ ገዳማትንም አቋቋመ፣ ታላላቅ ታምራትንም አደረገ፣ ሾላንም ተከለ፣ ዝግባንም ተከለ ብዙ እንጨቶችን ተክሎ ኤደም እንደምትባል እንደ አዳም ቦታ ውሃን በማጠጣት አደጉ የቤተ ክርስቲያን አፀድም ሆኑ ያስተማራቸውንም አፅናንቶአቸው ሄደ::

የረቡዕ

ከዚህ በኋላ ለማስተማር ሲመላለስ ወደ አባቶቹ ሀገር ወደ አባቱ መቃብር ገባ እዚያው ደርሶ ቤተክርስቲያን ሰራ ዕለቱን ስንዴ ዘርቶ፣ ወይን ተክሎ፣ ጽድንም ተክሎ፣ ወይራንም ተክሎ፣ ግራርን ተክሎ፣ በአንዲት ቀን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዕለቱን አደረሰ ስንዴውን ለመስዋዕት፣ ወይኑን ለቁርባን ዕለቱን በታምራት አድርሷል።

ስንዴውም ቆሮስ በሚባል መስፈሪያ ፱፱ ጫን ሆነ ይህም ለሚፈለገው ሁሉ አገልግሎት ሆነ፣ በጥዋት ተክሎ ለ፮ ሰዓት አድርሶ ከእሱም አሣምሮ ታቦታትን ቀርጾ ከዚህ በኋላ ያዘጋጀውን ታቦት ወደ ጳጳሱ ወስዶ ጳጳሱም እኒህን ታቦታት ባርኮ ስማቸውንም የእግዚአብሔር አብ ታቦት፣ የእመቤታችን ታቦት ብሎ ሰየማቸው።

ከቡራኬም በኋላ በ፮ ሰዓት ወደ አነፀው ቤተክርስቲያን ተመልሶ ታቦቶችን ከመንበሩ ላይ አስቀመጠ፣ የተከላቸው ወይራውና ግራሩ ለተልኮ ሥራ ደርሰዋል፣ የወይራ ፍሬም በቀንና በሌሊት ጸሎት የሚደረስበት መቁጠሪያ ሆነዋል፣ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ የተከላቸው እንጨቶች በስንዝር ፵ ክንድ ሆኑ ያንንም ደቀመዛሙርቱ በመጥረቢያ ቆርጠው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ለማእጠንት ሆነ።

ከዚህ በኋላ መላእክት ከሰማይ እጣን ከርቤ ከፃህልና ከዕዋዕ ጋራ ማዕጠንትን ከእርፈመስቀልም ጋር የካህናት ልብስና መጎናፀፊያ የሚያስፈልጉትን አልባሳት በሙሉ ይዘው ወረዱ።

ከዚህ በኋላ መጋቢት ሃያዘጠኝ በዘጠኝ ሰዓት የተመረጠውን መስዋዕት ከ፲፪ቱ መነኩሳት ጋራ አቀረቡ በዚያች ሶዓት ሥጋ ወደሙን የተቀበሉ ስዎች ብዛታቸው መቶ ሰባ ሺህ ይሆናሉ፣ ከእነርሱም በውሃ ተጠምቀው ከደዌ ሥጋ የተፈወሱ አሉ፣ ከደዌ ነፍስም የተፈወሱ አሉ፣ አባታችን አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ በጸሎቱ

የረቡዕ

የአመነጫቸው ውሃ ለቤተክርስቲያን አገልግሎትና ለጥምቀት ላልተጠመቁት አህዛብና ለታመሙት ተጠምቀው የሚድኑበት መድኃኒት ሆናቸው።

፮ በዚያች አካባቢ ብዙ አድባራትንና ገዳማትን አሠራ። እነርሱን ከአፀናቸው በኋላ ወደ ዝቋላ ገዳም ሄዶ እየጸለየ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት ሰባት ቀን ለነበተ።

፯ በሰባተኛው ቀን የአባታችን የገብረ መንፈስ ቅዱስን የገድላቸውን መጽሐፍ እየጸለየ ላለ አባታችን ገብረ መንፈስ ቅዱስ ፊቱ እንደ ፀሐይ እያበራ በሰማይ ላይ እንደ መብረቅ እያብለጨለጨ አባታችን ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወደ እርሱ መጥቶ ተገናኝተው እርስ በርሳቸው መንፈሳዊ ሰላምታን ተሰጣጡ።

፰ ድንቅ የሚሆን የእግዚአብሔር የተአምራቱን ኃይል ሲጨዋወቱ ዋሉ። ይህንን ሲጨዋወቱ ከዋሉ በኋላ ስለሃይማኖት አንስተው የእኛና የአባቶቻችን ሃይማኖት ለነፍስ የሚጠቅም፣ ከእግዚአብሔር ፊት የሚያደርስ የትኛው ሃይማኖት ነው ብሎ አባታችን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ጠየቀው።

፱ አባታችን ገብረ መንፈስ ቅዱስም መልሶ በብሩህ ገጽ ከእግዚአብሔር ፊት የሚያደርስ ሃይማኖት ሃይማኖትን ያቀኑ የሦስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንት ሃይማኖትና የአባቶቻችን የሐዋርያት ሃይማኖት ነው። እኔ ሥላሴን በአካላት ሦስት በመለኮት አንድ በአካል ትክክል የሆኑ በስልጣንም ትክክል የሆኑ ናቸው ብዬ አምናለሁ። የወልድ ልደቱ ሁለት ነው። በእውነት መጀመሪያው ያለ እናት ከአባት ተወለደ ሁለተኛ ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ያለ አባት ተወለደ እላለሁ፣ ከዚህ ሃይማኖት ያጎደለ፣ የጨመረም በእኔ ቃል እና በአንተ ቃል የተወገዘ ይሁን፣ ልጄ እስትንፋሰ ክርስቶስ ይህን ሃይማኖት ጠብቅ አለው።

፲ ከዚህ በኋላ አቡነ ዘበሰማያትን ጸልየው አባታችን ገብረ መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ተሰውሮ ወደ ሰማይ አረገ፣ አባታችን እስትንፋሰ ክርስቶስም አርባ ዕለት በጾምና በጸሎት ተወስኖ እዚያው ሰነበተ።

CamScanner

ምዕራፍ ፯

የረቡዕ

፩ ከዚህ በኋላ ወደ ጻድቁ አባታችን ተክለሃይማኖት ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም መጥቶ በመቃብሩ ላይ እየጸለየ ሰባት ቀን ቆየ በሰባተኛውም ዕለት አባታችን ተክለሃይማኖት ከቅዱሳን ልጆቻቸው ጋራ ወደ አባታችን እስትንፋሰ ክርስቶስ መጣ። እርስ በእርሳቸው ሰላምታ ተሰጣጡ። ግሩምና ልዑል የሚሆን የእግዚአብሔርንም ነገር የመለኮትን እና የትስብዕትን ምሥጢር፣ የተጋድሎንም ነገር ሲጨዋወቱ ቆይተው ከዚህ በኋላ አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ፊት ,የሚያደርስ ሃይማኖት የትኛው ነው? የእግዚአብሔር ወልድ ልደቱስ ስንት ነው? ብሎ ጠየቀ።

፪ ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖትም የእግዚአብሔር ወልድ ልደቱ ሁለት ነው፣ አንዱ ከአብ ሁለተኛው ከማርያም ተወለደ፣ የአባቶቻችን ሃይማኖት ይህ ነው።

፫ በመጨረሻ ዘመን መናፍቃን በሃይማኖት ላይ ፀብ ክርክርን ያመጣሉ፣ ሌላ ነገርንም ይፈጥራሉ ነገር ግን ከአባቶቻችን ሃይማኖት ያጎደለ ወይም የጨመረ ቢኖር የተወገዘ ይሁን አለው። ይህን ከአሉ በኋላ ጸሎትን ጸልየው ተሰነባበቱ።

፬ ከዚህ በኋላ አባታችን አቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ የሸዋን ገዳማት በሙሉ ዞሮ ከቅዱሳን መነኮሳትና ከስውራን መነኮሳት ቡራኬን ተቀበለ። ጸሎት እየጸለየ የብዙ ብዙ የሚሆኑ አሕዛብን እየመከረ፣ እያስተማረ አጠመቀ።

፭ ባሉትን እዚያው ሰርቶ በአካባቢው ወይንን ተክሎ የአካባቢውን ሕዝብ ሁሉ በቅዱስ ወንጌል ስብከት የቸገፀጯቱ ሊቃውንት ሃይማኖትና የአባቶቻችን ሐዋርያት ሃይማኖትን አስተምሮ አሳመነ።

፮ ከዚያም እየጸለየ እየሰገደ ለቤተክርስቲያን እያገለገለ በገድል እና በቀኖና በንጽህና ኖረ ከአንድ ገዳም ወደ አንድ ገዳም በሰረገላ እየተመላለሰ ወደ ወደደው ይሄዳል።

፯ የአባታችን የአቡነ እስትንፋሰ ክርስቶስ መልኩ ቁመቱ እንደ ሸንበቆ ያማረ ፊቱ እንደ ጽጌረዳ ቀይ ጸጉሙ እንደ ሐር የተፈተለ ነው። ግርማውም እንደ አንበሳ

የረቡዕ

፰ ግርማ ያስፈራል መዓዛውም ናርዱ ጵስጥቄስ አልባስጥሮስ እንደሚባል ዋጋው ብዙ እንደሆነ ሽቱ ያማረ ነው። ማዓዛውም ዱሩን በመሉ ይሞላ ነበር፣ ፊቱም እንደ መልአክ እግዚአብሔር ፊት ይመስላል፣ ጸመም እስከ ደረቱ የወረደ ነው። የአባታችን የአቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ ስም የጣፈጠ ነው።

፱ ዳግመኛም ለታመሙት መድኃኒት፣ ለእውራን ብርሃን፣ ለአንካሶች መሄጃ፣ ለምፃሞችን የሚያነፃ፣ ለነጋዴዎች ፀጥታ ነው። በራሱም ላይ በትምህርተ መስቀል ምልክት አክሊል አለው ይኼውም የሰሌን ቆብ ነው፣ መጠምጠሚያም ከመታጠቂያ ጋራ አለ፣ በአድባራትና በዋሻ፣ በገዳማት ያሉ መነኮሳት ለጠላት ዲያብሎስ የማይቸነፍ አሸናፊ አባ እስትንፋስ ክርስቶስ ልዑል ነው፣ አባ እስትንፋስ ክርስቶስ የመንፈስ ቅዱስን ቅባት የተቀባ የከበረ ነው አሉ።

ፈጽመው እንቅልፍን የናቁ ሁለቱ ቅንድቦቹ ያማሩ ናቸው፣ ሁለቱ አይኖቹም እንደ አጥቢያ ኮከብ የሚያበሩ ዘወትር መጸሕፍትን ለማንበብ ለመጻፍ የሚመለከቱ ወደ ሰማይ እየተመለከቱ እንባኜ የሚያፈሱ ናቸው።

፲ አባታችንም በሚጸልይበት ጊዜ ሰማያዊ በር ተከፍቶለት የሰማይን ምሥጢር ያያል ጆሮቹም የመጽሐፍትን ቃልና የመድኃኒታችንን ቃል ኪዳን ቃሉን ይሰማሉ። የለመለመ ሽፋሽፍቶቹም ከዐይኑ ምንጭ እንደ ሰን ውሃ ፍላሽ ዕንባን ያፈላሉ፣ አፍንጫውም ዘወትር የቅዱሳንን መዓዛና የመስዋዕት መዓዛ፣ የእጣን መዓዛ፣ ዘወትር ያሸታል፣ ከንፈሮቹም ያለእረፍት የመጻሕፍትን ቃላት ያነባሉ፣ ይተረጉማሉ፣ በአፉም ወይንን የማር ጠጅን፣ ወተትን አልጠጣም፣ የበሬ ሥጋን፣ የላም ሥጋን፣ የበግ ሥጋን፣ የፍየል ሥጋን፣ የአዟ ሥጋን ሌሎችንም የመላስለ የእንስሳት ሥጋን፣ ያለ ክርስቶስ ሥጋና ደም አልቀመስም፣ አንደበቱም ሽንኵላን፣ ሠሜትን አልተናገረም፣ ዘወትር ብሉያትንና ሐዲሳትን ያለ እረፍትና ያለማስታጎል በቀንና በሌሊት ያነባል እንጅ።

CamScanner

የረቡዕ

ቃሉም ያማረ ነው ድምፁም ቃጭል ነው። በመልካም እስትንፋሱም በታመመ ሰዎች ላይ እፍ ባለ ጊዜ ፈጥኖ ይፈውሳቸዋል፣ ጉሮሮውም በውሃ ጥም የደረቀ ሆኖ ሳለ በውስጡ በጸሎት ውሃ ያጠጣዋል መልካም አንገቱም ያማረ ሆኖ ሳለ በላዩ ላይ አስኬማና ቅናት አለበት፣ በትከሻውም ላይ የቅዱሳን ቀንበር አጽፍ የተጫነ ነው። ብዙ መጻሕፍትም አሉት።

ዘወትር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ግርፋት አስቦ ፱ ሺህ ፱ ሺህ ጊዜ ዕራሱን ይገርፋል፣ በደረቱም ላይ የሃይማኖትና የጥበብ ሞጣሕት ወንጌልን፣ ሥእልን አደረገ፣ የእሱንም ሥራ እናውቅ ዘንድ ትሩፋትንም እንቆጥር ዘንድ ባሰብን ጊዜ መረዳት ያቅተናል፣ ተጋድሎው ከባህር አሸዋና ከዝናብ ነጠብጣብ ከከዋክብትም ፈጽሞ ይበዛል።

ስንቱን እንናገራለን፣ ነገር ግን ጥቂት ተናግረን ዝም እንላለን እንጅ እግዚአብሔርም እጅግ አከበረው ከፍ ከፍ አደረገው፣ የአንዱ እግሩ መርገጫውን ያህል ሰማይና ምድር ፀሐይና ጨረቃ ሰውም መጠኑ አይሆኑም።

ነቢያትና ሐዋርያት ዘመዳችን ይሉታል፣ መላእክትም በክንፋቸው ይሸከሙታል፣ ይሰውሩታልም፣ እመቤታችን ማርያም ወዳጁ እንደምን አለህ ትለዋለች።

ከእለታት በአንድ ቀን አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ በጸሎት ላይ ሳለ፣ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ከብሩህ ደመና ጋራ ወደ እሱ መጥቶ ና በዚህ በዳመና ላይ ውጣ አለው፣ አባታችንም በዳመና ላይ ሲወጣ ቅዱስ ሚካኤል ወስዶ ወደ እግዚአብሔር አደረሰው።

እግዚአብሔርም ባረከውና አብርሃምንና ይስሐቅን፣ ያዕቆብን ፲፭ ነቢያትን ፲፪ ሐዋርያትን ጻድቃንና ሰማዕታትን ሁሉ ሰብስቦ በየማህባራችሁ በየወገናችሁ መርቁት፣ ባርኩት አላቸው።

CamScanner

የሬቡዕ

፮ ተነስታችሁም ከእናንተ በኋላ የተወለደውን በገድል ከእናንተ የሚበልጠውን ተመልከቱት፣ እኔም ከእሱ ጋራ ከብሬ እኖራለሁ እናንተም ከእሱ ጋራ በአንድነት ነግላችሁ ትኖራላችሁ አላቸው።

፯ እነሱም ባረኩት አከበሩት፣ ከፍ ከፍ አደረጉት፣ እጅግ አደነቁትም።

፰ ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልአኩን እስትንፋስ ክርስቶስን ወደ ምድራዊት ኢየሩሳሌም አወርደህ ወደ ተወለድክባት ቦታ፣ ወደ ኖርክባት ቦታ አድርስህ አሳየው አለው።

፱ ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ በክንፉ ተሸክሞ አውርዶ ከቤተልሔም አደረሰው፣ ከዚያ በኋላ ወደ አደገበት ሀገርና ውሃን ወደ አፈለቀበት ሀገር ሄደ በዚያም ብዙ ምሥጢርን አየ፣ እንደገናም ጌታችን ታምራትን ወደ አደረገበት ቦታ ሁሉ ሁለቱም በአንድነት ሄዱ ከዚህም በኋላ ወስዶ ወደ ጌታችን መቃብር ወደ ጎል ጎታ አደረሰው።

ምዕራፍ ፰

በዚያም ሰገደና እረጅም ጸሎት ጸልዮ መሐሪ ይቅር ባይ ከሚሆን ከፈጣሪ ዘንድ ምህረትን ለምኖ የኢትዮጵያንም ኃጢአት አስተሰረየ፣ ጌታችንም ስምህን የጠራውን ዝክርህን ያዘከረውን በዓልህን ያከበረውን ምሬለሃለሁ አለው፣ ወደ ተሰቀለበት ወደ ቀራንዮ ቦታ ወደ ተቀበረበት ወደ ጎልጎታ ወደ ተጠመቀበት ወደ ዮርዳኖስ ባህር ደርሶ ጸሎቱን ጸልዮ ብዙ ድንቅ ድንቅ ምሥጢራትን አየ፣ ወደ ደብረ ቁስቋምም ሄደ።

በዚያም እንደዚሁ ብዙ ታምራትን አየ ከዚህ በኋላ ወደ አባ እንጦንስና ወደ አባ መቃርስ ገዳም ወደ አስቂጥስ ሐዶ በዚያ የምንኩስና ሥርዓትን ተማረ ዳግመኛ ም ወደ ደብረ ምጥማቅ አልፎ በዚያ ሯ ቀን ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም

የረቡዕ

ጋራ ስንብቶ ድንቅ ታአምራትን አየ፣ እናቱንና አባቱን ፲ ሺ ነፍሳትን ነቢያትን፣ ሐዋርያትንም በዚያ አያቸው::

ከአምስት ቀን በኋላ ወደ ጳጳሱና ወደ ሊቀ ጳጳሱ ወደ ደጋጎች ካህናትም ሄዶ ተባረከ ወደ ፲፩ቱ ነቢያት መቃብር ወደ ፲፪ቱ ሐዋርያት መቃብር ሃይማኖትን ያቀኑ ወደ ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት መቃብር ሄዶ አየ:: ከእነሱም ቡራኬ ተቀብሎ ተመልሶ ወደ ኢያሪኮ ሀገር ከባህር ዳር ደርሶ አንዱንዋናተኛ አሻግረኝ ብሎ ለመነው እሱም እንቢ አለው፣ ከዚህ በኋላ አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ ከባህር ዳር ቁሞ ጸለየ ጸሎቱን ከፈጸመ በኋላ በሀሩን እንደ ደረቅ በእግሮቹ እየረገጠ እግሮቹ ሳይርሱ ተሻገረ::

ከዚያ ሄዶ አርማኒያ ወደምትባል ሀገር ወደ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ መቃብር ደረሰ፣ በዚያ ሰባት ቀን በጾምና በጸሎት ሰነበተ::

ከሰባት ቀን በኋላ አባታችን አቡነ ኤዎስጣቴዎስ ወደ አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ መጥቶ የመለኮትን ምሥጢር እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ድንቅ ሥራ ተጨዋወቱ::

ከዚህ በኋላ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ አባታችን እስትንፋስ ክርስቶስን ልጁ የያዝከውን ሃይማኖት ጠብቅ፣ የጀመርከውንም ገድል በርትተህ ፈጽም አለው::

ዳግመኛም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደነገረህ ሁለት ልደት በማለት ከዚህ ሃይማኖት አትቀንስ፣ አትጨምር ይህን ብሎት ወደ ገነት አረገ::

ከዚህ በኋላ አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ ጸሎት ጸለየ፣ ከሱ ጋራ የነበረ የእግዚአብሔር መልአክ መልሶ ወደ ኢትዮጵያ ምድር ደብረ ዛብሒል ወደምትባል ቦታ አደረሰው ከዚያ ደርሶ ድንቅ ታምራትን አደረገ፣ ውሃን ከአለት ላይ አመነጨ በዚያም ፲፪ በሽተኞች ነበሩ፣ በዚያ ውሃ አጥምቆ እነዚያን ድውያን ፈወሳቸው::

CamScanner

የሬቡዕ

ከእለታት በአንድ ቀን ወይን ተክሎ ያም ወይን በተተከለበት ዕለት ደርሶ ለማህበሩ ምግብ ሆኖአል::

ዳግመኛም እነሆ የሚለግድበት ሥዕል ነበረች ያችም ከግብፅ የወጣች ሉቃስ የሳላት የእመቤታችን የማርያም ሥዕል ነበረች ዋሻ ሰርቶ በዚያ አስቀመጣት፣ ያችም ሥዕል ድንቅ ድንቅ ታምራት ታደርግለት ዛብሔል ከምትባል ቦታ ዘወትር ታናግረው ነበር፣ ብዙ ሰዎችንም አስተምሮ አጥምቆ አመነኮሳቸው በዚያም በአት ሰርቶ በውስጧ በጾምና በጸሎት ወደ እሱ የመጡትን በማስተማር በመልካም ተጋድሎ ተፀምዶ ተወስኖ ኖረ፣ የሰዶምና የገሞራ ሰዎች የሠሩትን ኃጢአት የሚሠሩ በሥራ እነሱን የመሰሉትን የብዙ ኃጢአተኞችን ሰዎች ነፍሳት ከሲኦል አውጥቷል በእየለቱ ከዚያ ቦታ ፷፪ ነፍሳትን ከሚነድ እሳት ያወጣ ነበር::

፲፩ ከዚህ በኋላ ቀኖና ይዞ በባህር ውስጥ ጠልቆ ዘወትር ይጸልይ ጀመር በሄደበት - ሀገር ሁሉ ከባህር ውስጥ ገብቶ ይጸልያል ከእለታት ባአንድ ቀን አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ አቤቱ ::

፲፪ የማርፍበትን ቦታ ሥጋዬ የሚቀበርበትን ቦታ ግለፅልኝ ብሎ ጸለየ ከዚህ ጸሎት በኋላ ገብርኤል መልአክ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ መጥቶ አባ እስትንፋስ ክርስቶስ ሆይ የአባትህ አባት ከሸዋ ሀገር መጥቶ ታቦተ እግዚአብሔር አብን ወደ ተከለበት ወደ አባ ሙሴ ደብር ወደ አባትህና ወደ እናትህ ቦታ ዳውንት ወደምትባል ሀገር ሂድ ብሎ የዕረፍቱን ቦታ ነገረው::

፲፫ ዳግመኛም የእግዚአብሔር መልአክ በጎዳና መካከል ብዙ እንጨቶች ባሉበት ከሰው የተለዩ ተመርጠው የተሰወሩ ብዙ መነኮሳት ወዳሉበት በውስጡም የአባ ሙሴ ሀንፃ ተዘግቶ ወደ ተሰወረበት ይህ የተሰወረ ሀንፃ ወዳለበት ከላይም ገደል ወደ ሆነ ገዳም ሄደህ የአባቶችህን አጥንት ጠብቅ አለው:: በዚህች ቦታ ሞገስንና ክብርን ታገኛለህ ይህችንም ቦታ የእግዚአብሔር ወዳጆች ስውራን መነኮሳት ይጠብቋታል፣ የምስጋና መስዋዕትም ይሰውበታል፣ በዚህችም ቦታ ትቀበራለህ:: አባ እስትንፋስ ክርስቶስ ሆይ በዚህም ቦታ ሥጋህ ይቀበራል አለው::

CamScanner

የረቡዕ

፲፬ ሊቀመላእክትም ቅዱስ ገብርኤል ይህን ነግሮት አረገ፣ አባታችን አስትንፋሰ ክርስቶስም ከዚያ ወደ ምሥራቅ አለፈ፣ የአገሩም ሰዎች ባዩት ጊዜ ባንድነት እልል እያሉ ተቀበሉት፣ በዚያም ድንቅ ታምራትን አደረገ፣ በዚያም ቤተክርስቲያንን አሠርቶ የሃያ አራቱ ከህናተ ሰማይን ታቦት አስገባ፣ በዛብሔልም ምድር ታላቅ ታምር አደረገ፣ ብዙ አመታትንም ተቀመጠ።

፲፭ ከዚያም ተነስቶ ሮሐ ወደምትባል ምድር ደርሶ የቅዱስ ላሊበላንና የቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስን፣ የቅዱስ ነአኩቶለአብንም መቅደስ ላመ፣ ከቅዱሳን ቦታ ሁሉ ተባረከ።

፲፮ የዛች ሀገር ካህናትም በታላቅ ክብር ተቀበሉት፣ እግዚአብሔር በተሰደደበት ሀገር ለአቡነ አስትንፋሰ ክርስቶስ ያደረገለትን ድንቅ ታምራት ሰምተዋልና ፮ ቀንም ሮሐ በምትባል ሀገር በላሊበላ መቃብር ሰንብቶ በዚያ ምልክትንና የተሰወረውን ምሥጢር አገኘ፣ ከዚያ ወደ ይምርሐነ ክርስቶስ ቦታ ሄደ፣ ሰባት ቀን ሰንብቶ ምልክት አገኘ ለሰው ልጅ መናገር የማይቻለውንም ምስጢር አየ።

፲፯ ከዚያ ተነስቶ ጻድቁ ነአኩቶለአብ ወደ ተሠወረበት ቦታ ደርሶ ሰባት ቀን ከዚያ ሰነበተ፣ ከሰባት ቀን በኋላ አባታችን አቡነ አስትንፋሰ ክርስቶስን ነኩቶለአብ የተሠወረበትን ቦታ መልአክ እየመራ አደረሰው።

፲፰ በደረሰ ጊዜ እርስ በርሳቸው በከበረች ሰላምታ እጅ ተነሣስተው በደስታ የእግዚአብሔር ጌትነቱን፣ ለቅዱሳንም የሚደረግላቸውን ታምራት ሲጨዋወቱ አንድ ቀን ዋሉ።

፲፱ ከዚህ በኋላ ጸሎት ጸልየው ነአኩቶለአብ አቡነ አስትንፋሰ ክርስቶስን ሸኘው፣ አባታችንም ለሰው ሰለማይነገር ስለተጫዋወቱት ምሥጢር እየተደሰተ ወጣ።

ያገሩም ሰዎች ጻድቁ አስትንፋሰ ክርስቶስ ወደ እነሱ ስለመጣ ደስ አላቸው፣ የክርስቶስ ሥጋና ደም በእጁ እንቀበል ዘንድ ይህን ጻድቅ መምህር ወደ እኛ ያመጣው እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፣ በእጁም እንመነኩስ ዘንድ ያደለን እሱ የተመሰገነ ይሁን እያሉ፣ ብዙ ሰዎች መጥተው በቆብና በአስኬማ በቅናት

ቀሲስ የሱስ መላኦ

ከእሱ ተወለዱ፣ ስለ ስብከቱና ስለ ጽድቁ፣ ስለ ትሩፋቱ ዝናው በየሀገሩ ሁሉ ተሰማ ብዙዎች ወደ እሱ መጥተው እያመሰገኑት እያደነቁት በፍቅር እጅ ነስተው ከእግሩም ላይ ወድቀው እጅ መንሻ አቀረቡለት፣ እሱም ከእነሱ ምንም አልተቀበለም እግዚአብሔርም አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስን ዘወትር ይመግበው ነበርና::

ምዕራፍ ፱


፩ ከዚህ በኋላ አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ ወደ ትግራይ ሀገር ከዘጠኙ ቅዱሳን በረከት ይቀበል ዘንድ ሄደ፣ ደብረ ዳሞ ደርሶ በትምህርተ መስቀል አማትቦ ያለ ገመድ ከደብረ ዳሞ ተራራ ላይ ወጣ በተራራ ላይ ፵ መዓልትና ፵ ሌሊት በትጋት በመጾም ሳይቀመጥ ቆሞ እየጸለየ፣ እህል ሳይቀምስ ሰነበተ::

፪ ከዚህ በኋላ አቡነ አረጋዊ አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስን ተገናኘው፣ ከዚያ እርስ በእርሳቸው ሰላምታ ተሰጣጥተው የእግዚአብሔር ገናንነትና ተጋድሎ ያላቸው የመነኮሳት ታምራትና ሃይማኖት ተጨዋወቱ፣ ሁለቱም አቡነ ዘበሰማያት ከጸለዩ በኋላ አቡነ አረጋዊ ተሠውሮ ወዳለበት ቦታ ተመልሶ ሄደ::

፫ አባታችን አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስም ወደ ደብረ አክሱም ሄዶ ጽዮንን ተሳለማት፣ ጽዮንም የልጇ የክርስቶስ እስትንፋሱ የሆንክ የከበርክ መናኝ ሆይ እንደምን አለህ አለችው አባታችን እስትንፋስ ክርስቶስም የእግዚአብሔር የህጉ ማደሪያ የሆንሽ ጽዮን ሆይ ሊቀ ነብያት ሙሴ በደብረ ሲና ፵ ማዓልት እና ፵ ሌሊት በጸመ ጊዜ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእኛ የወረድሽልን እኛን ለማዳን ለሙሴ የተሰጠሽ ለአንቺ ሰላምታ ይገባሻል::

፬ ከዚህም በኋላ ወደ እኛ ወደ ኢትዮጵያ ምድር መጣሽ ህማና ስርአት ከአንቺ ይወጣል እና ዛሬ ተገለጭልኝ ብሎ ጽዮንን አመሰገናት፣ በዚያን ጊዜ ተገልጻለት በማየቱ ደስ ተሰኝቶ እጅም ነሳት እሷን አስመስሎ ሁለት ጽላትን እንደ ወልድ ልደት ምሳሌ ሁለት አድርጎ ቀረጸ::

CamScanner



ሥዕል 9፦ ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስን ቆዳውን ገፈው በቆዳው ውስጥ አሞሌ ጨው (ስልቻ) ሞልተው እንዳሸከሙት።

ውም ሆነ። እጅ ነሣው እንባውንም ጠረገለት። በዚህ ደመና ተቀመጥ በሰላምም ወደ ወንድሞችህ ሐዋርያት ያደርስሃል። እኔም በምትጥሩበት ቦታ ሁሉ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ። አባቱ የመረጣችሁ አምላክነቱን ለዓለም ሁሉ ልታስተምሩ ነውና አለው። ጌታችንም በታላቅ ምሥጋና ከእነርሱ ወረገ።

69. ቅዱስ ቶማስም እግዚአብሔር እንዳዘዘው በታላቅ ክብር በደመና ተጫነ። ደመናይቱም ተሸከመችው። ኒአበአንዲን ኢንሰስ ወደተባለች ተራራም አደረሰችው። ሐዋርያትንም ተሰብስበው አገኟቸው። ቅዱስ ጳውሎስም በመካከላቸው ነበር። የጌታችን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም ነበረች። መንፈሳዊ ሰላም ታንም ሰላም ተባባሉ። እግዚአብሔር በእጃው ያደረገላቸውንም ድንቅ ሥራ አሰቡ። እርስ በእርሳቸው ተሰብስበውም ሰማንያ ቀን ተቀመጡ። ምስጋና የሚገባው እግዚአብሔርንም አመሰገኑት። ክብርና ምስጋና እስከ ዘለዓለሙ ድረስ ለእርሱ ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን፤ አሜን።

ክፍል ሦስት

1. አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚነበብ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያው የሚሆን የቅዱስ ቶማስ ምስክርነቱና በእግዚአብሔር ፈቃድ ግንቦት ሃያ ስድስት የፈጸመው ተጋድሎ ይህ ነው። ጸሎቱና በረከቱ ከወዳጁ ከ_____ ጋር ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን።

2. ቅዱስ ቶማስ ወደ ሕንድ በወጣ ጊዜም በሃይማኖት አጸናቸው። የቅዱስ ወንጌልን ሕግም አስተማራቸው። ቆዳውን ያስገፈፈው ሉክዮስም ነበር። በአንገቱ አድርጉም ብዙ ዘመን በየሀገሩ ይመላለስ ነበር። ከሙታን ተለይቶ ይነሡና ይፈወሱ ነበር።

ትካት ወተአምኖ ወአንገፈ ላሆ ወይቤሎ ንበር ዲበ ገዘንቱ ደመና ወውአቱ ያበጽሐክ ኀበ አኃዊክ ሐዋርያት በሰላም አነ እሄሉ ምስሌክሙ ውስተ ዮሉ መካን ኀበ ትሄልጢ እስመ አንትሙ እለ ኀረየክሙ አቡየ ከመ ትስብኩ ውስተ ዮሉ ዓለም አምላክነየ፣ ወነገርን እግዚእነ እምኔሆሙ ውስተ ሰማይ በዓቢይ ስብሐት።

፷፱. ወቅዱስ ቶማስ ተጽዕነ ዲበ ደመና በዓቢይ ስብሐት በከመ አዘዞ እግዚአብሔር። ወያረቶ ደመና ወአብጽሐቶ ኀበ ደብረ ኒአበአንዲን ኢንሰስ ወረከቦሙ ለሐዋርያት ገቡዓን። ወቅዱስ ጳውሎስ ማእከሎሙ ወማርያም ወላዲተ አምላክ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወተአምኑ ተአምኖ መንፈሳዊተ ወተዘክሩ መንክረ ዘጎበረእግዚአብሔር በእደዊሆሙ። ወነበሩ ፫ዕለተ ገቡዓን በበይና ቲሆሙ ወሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ዘለዓቲ ስብሐት ወክብር ወአኮቴት እስከ ለዓለመ ዓለም አሜን ወአሜን።

ክፍል ፫

፸. በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ዝንቱ ስምዐ ለቅዱስ ቶማስ ሐዋርያሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወገድሉ ዘፈጸመ አመ ፳ወ፮ ለወርኃ ግንቦት በሰላመ እግዚአ ብሔር ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስለ ፍቁሩ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፸፩. ወኮነ እምድኅረ ወፅአ ቅዱስ ቶማስ ኀበ ሀገረ ሕንደኪ ወሰበከ ለሙ በአሚን ወዜነምሙ ሕገ ወንጌል ቅዱስ። ወለክዮስኒ መኰንን ዘዝሐቀ ማዕሶ። ወነበረ ብዙኀ መዋዕለ ይጸውር ዲበ ክሣዱ ወያንሶሱ ላዕለ ዮሉ በሐውርት። ወያነብር ላዕለ ምውታን ወድውያን ይትነሥኡ ወይትፈወሱ።

3. ጌታችንም ልቡናቸውን ገለጠላቸውና አመኑ። ቤተ ክርስቲያንም ተሠራላቸው። የሃይማኖትን ሕግም አጸናላቸው። ኤጲስ ቆጶሳትን ሾሳው ስትንና ዲያቆናትንም ሾመላቸው፤ ከተቀደሰው ምስጢርም ሰጣቸው። በጌታችን ሰላምም ከእነርሱ ወጣ። ጌታችንም ተገለጠላቸው ቆዳውም ተመልሶ እንደ ጥንቱ ሆነ። ከዚህ በኋላ የመቂዶንያ አውራጃ ወደምትሆን ወደ ሕክቲ ሄደ። በዘያም እግዚአብሔርን ስለማውቅ አስተማረ። መካንንቱም በሰመ ጊዜ ልቡናቸው ቱጣን ተሞላ። ይዘውም ወደ እስር ቤት ጨመሩት።

4. የንጉሡ ሚስት ጥርጥባንያኒና ልጁ ምርሐናም ወደ እስር ቤቱ ወደ እርሱ መጡ። ብዙ ምእመናንም ተከተሏቸው በሩም ተከፈተ ላቸው ሐዋርያውንም ጠሩት፤ ወደ እነርሱ መጣ። ቅዱስ ቶማስም ወንድሞቼ፣ ልጆቼና የእግዚአ ብሔር አገልጋዮች ወዳጆቼ ሆይ ዛሬ ነገሬን ስሙ። ለእናንተም የትምህርቴ መጨረሻ ነው። ከዚህች ዕለት በኋላ እኔ በዚህ ዓለም በሥጋ ወደ እናንተ የምመለከት አይደሁለም። እነሆ እግዚአ ብሔር ከዚህ ዓለም ነፃ ሊያወጣኝ ፈቅዷልና። ከዚህ ድካም ወደ ዕረፍት ያወጣኛል።

5. እርሱ ሰይጣንን ከማምለክ ያድነን ዘንድ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጠ። ለሐዋርያኑትም መረጠን በዓለም ሁሉ በስሙ እናስተምር ዘንድም አዘጋጀን። እነሆም ተጋድሎየን ፈጸምኩ። እንዳዘዘኝም መልእክቱን አደረስሁ። አሁንም ከዚህ ዓለም ስቃይ ሊያሳርፈኝ ወደደ። በእርሱ ዘንድ የተዘጋጀ ዋጋዬንም ሊሰጠኝ ወደደ። እርሱ ሀብቱ ብዙ ነውና። ለሚለምኑት ሁሉ ሀብቱን እንዲሁ ይሰጣልና። እኔም የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ ነኝ፤ ፈቃዱንም አደርጋለሁ።

6. እነሆም ፈቃዴ ከእኔ እንደሰማችሁት ነው ተጠበቁ። በልቡናችሁም ወደ እናንተ እንዳ ይቀርብ ለሰይጣን መንገድ አትስጡ። በሰማያዊ መንግሥቱ ይቀበላችሁ ዘንድ ዳግመኛ የጌታችንን

1. እግዚእነ ከሠተ አልባቢሆሙ፡ ወአምነ ወሐነፀ ሎሙ ቤተ ክርስቲያን ወአጽንዓ ሎሙ ሕገ ሃይማኖት። ወሜመ ሎሙ ኤጲስ ቆጶሳተ ቀላውስተ ወዲያቆናተ ወወሀቦሙ ምሥጢራተ ቅድሳት ወወፅአ እምኀቤሆሙ በሰላመ እግዚእነ። ወእግዚእነ ተርእየ ሎሙ ወገብአ ማዕሰ ከመ ትካት። ወሖረ እምድኅረ ገዝኑ ኀበ ሀገረ ሕክቲ በዲበ መቄዶንያ። ወሰበከ ውስቴቶሙ በአእምሮ እግዚአብሔር ወሶበ ሰምዑ መኳንንት መልዓ መዓት ውስተ አልባቢሆሙ አንገዘ ወወደይዎ ውስተ ቤተ ሞቅሕ።

2. ወጥርጥባንያኒ ብእሲተ ንጉሥ ወምርሐና ወለቱ በጽሓ ኀቤሁ ኀበ ቤተ ሞቅሕ ወተለውዎን ብዙኃን መሃይምናን፤ ወተርኅወ ሎሙ አንቀጽ ወጸውእዎ ለሐዋርያ ወመጽአ ኀቤሆሙ ወይቤ ሎሙ ቅዱስ ቶማስ አ አኃውየ ወውሉድየ ወፍቁራንየ አግብርተ እግዚአብሔር ስምዑ ነገርየ ዮም ወተፍጸመት ትምህርትየ ለክሙ። እስመ አነ አኮ እሬኢ ኀቤክሙ ውስተ ዝንቱ ዓለም እምድኅረ ዛቲ ዕለት ወአነሂ በሥጋ። ወናሁ እግዚአብሔር ፈቀደ ከመ ያግዕዘኒ እምዝንቱ ዓለም። ወያወፅአኒ እምዝንቱ ድካም ውስተ ዕረፍት።

3. ወውእቱ መጠወ ነፍሶ በእንቲአነ ከመ ያድኅነነ እምአምልኮ ሰይጣን። ወኀረየነ ሎቱ ሐዋርያቲ ወአስተዳለወነ ከመ ንስብክ በስመ ውስተ ዙሉ ዓለም ወናሁ ፈጸምኩ ተጋድሎ ወአብጻሕኩ መልእክትየ በከመ አዘዘኒ። ወናሁ ፈቀደ ከመ ያዕርፈኒ እምሕማመ ዝንቱ ዓለም። ወየሀበኒ ዕሤትየ ዘድልው ኀቤሁ እስመ ውእቱ በዓለ ብዙኀ ሀብት። ወይሁብ ጸጋሁ በከንቱ ለእለ ይስእልዎ። ወአነሂ ገብሩ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወገባሬ ፈቃዱ።

4. ወናሁ ፈቃድየ ዘከመ ሰማዕክሙ እምኔየ ተዓቀቡ ወኢታርእዩ ፍኖተ ለሰይጣን ውስተ አልባቢክሙ ከመ ኢይቅረብ ኀቤክሙ። ወኩኑ ንቁሐን ትጹንሑ ዳግመ ምጽአቶ ለእግዚእነ ከመ ይትመጠወክሙ ውስተ መንግሥቱ ዘበሰማያት።

እየተናገረም ሴቶቹን ተዋቸው። ወደ እስር ቤትም ገባ። እነርሱም እያለቀሱ ወጡ። ቅዱስ ቶማስን ይገድሉት ዘንድ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ ዐወቁ። ወደ እስር ቤት በገባ ጊዜም የእስር ቤቷ በር ተዘጋች፤ እንደቀደመችውም የተዘጋች ሆነች።

7. ጠባቂዎችም በተመለከቱ ጊዜ እርስ በእር ሳቸው ጮሁ፤ እንዲህ እያሉም ፈጽመው አደነቁ። ይህ ጠንቋይ ሰው የእስር ቤቱን በር ከፈተ በዚህ ውስጥ ያሉትን ሁሉ ሊያስወጣም ወደደ ነገር ግን መንገድ አላገኘም ነና ወደ ንጉሡ እንሂድ ስለዚህ ነገር ስለሰውየው፤ ስለልጁና፤ ሚስቱ ወደ እርሱ ስለመጡ ስለ ሁለቱም እንንገረው አሉ።

8. ይህን ሲነጋገሩ ቅዱስ ቶማስ ምንም አልመለሰላቸውም። ሲነጋም ወደ ንጉሡ ሄዱ። ይህን ጠንቋይ ከዚህ የእስር ቤት አውጣው። ከሌላ የእስር ቤትም አድርገው። እኛ የምንጠብቀው አይደለምና። እነሆ ሁለት ጊዜ የእስር ቤቱ በሮች ተከፍተው አየን። የሚከፍታቸውም እርሱ ነው። ሚስትህ፤ ልጅህም ዘወትር ወደ እርሱ ይመጣሉ አሉት።

9. ንጉሡም ወደ እስር ቤቱ በር ተመለከተ፤ በር የተቆለፈ እንደሆነም ተረዳ። እናንተ ውሸተኞች ናችሁ። ሚስቴም ልጄም ከእርሱ አልደረሱም አላቸው። እነርሱ ግን ወደ እርሱ እንደመጡ ማሉለት። ንጉሡም በፍርድ አደባባይ ተቀመጠ። ቅዱስ ቶማስን ወደ እርሱ እንዲያመጡትም አዘዘ። ልብሶቹን ወስደው አስታጥቀውም በንጉሡ ፊት አቆሙት። ንጉሡም አንተ ጌታ ነህ አገልጋይ ነህ አለው። ቅዱስ ቶማስም የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነኝ በእርሱ ላይ የአንተ ሥልጣን የለህም አለው።

10. ንጉሡም ከሀገርህ ሸሽተህ ወደዚህ ቦታ ለምን መጣህ አለው። ቅዱስ ቶማስም ይህን ሕዝብ ከስህተት እመልሰው ዘንድ ወደዚህ ቦታ መጣሁ፤ እኔም ከዚህ ዓለም እለያለሁ አለው። ንጉሡም የአምላክህ ስም ማን ነው? ሀገርህስ

ወእንዘ ይብል ዘንተ ነደጎን ለአንስት ወቦአ ውስተ ቤተ ሞቅሕ፤ ወእማንቱኒ ወፅኣ እንዘ ይበክያ ወአእመራ ከመ መጠወ ርእሶ ለመኳንንት ይቅትልዎ ለቅዱስ ቶማስ። ወሶበ ቦአ ቤተ ሞቅሕ ተዓወት ናኒታ ለቤተ ሞቅሕ፤ ወተዓወት ከመ ትካት።

፮. ወሶበ ርእዩ ዓቀብት ከልሉ በበይናቲሆሙ ወተደሙ ወአንከሩ እንዘ ይብሉ ወገንቱ ብእሲ መሠርይ አርኃወ ኖኅተ ቤተ ሞቅሕ ወፈቀደ ከመ ያውፅእ ኵሎ ዘሀለዉ ውስቴቱ ወኢረከበ ፍኖተ ንዑ ንሑር ኀበ ንጉሥ ወንንግሮ በእንተ ዝንቱ ወበእንተ ብእሲቱ ወወለቱ ወለክልኤሆን ዘበጽሐ ነቤሁ።

፯. ወእንዘ ይትናገሩ ኢያውሥአመ ቅዱስ ቶማስ ወኢምንተኒ። ወሶበ ኮነ ጽባሐ ሖሩ ኀበ ንጉሥ። ወይቤልዎ አውፅኦ ለዝንቱ መሠርይ እምዝንቱ ቤተ ሞቅሕ እስመ ንሕነ አኮ ዘነዓቅቦ። ወናሁ ክልኤ ጊዜ ርኢነ ኖኅተ ቤተ ሞቅሕ ርኅወ። ወውእቱ ያርኅዎሙ ወብእሲትከኒ ወወለትከ ኵሎ አሚረ ይበጽሐ ነቤሁ።

፰. ወንጉሥሰ ነጸረ ኀበ አንቀጸ ቤተ ሞቅሕ ወአእመረ ከመ ኮነ ማኅተሞ ዘተኀትመ። ወይቤሎሙ አንትሙ ትኄስዉ ወኢበጽሐት ብእሲትየ ነቤሁ ወኢወለትየ ወውእቶሙኒ መሐሉ ሎቱ ከመ በጽሐ ነቤሁ ነበረ ንጉሥ ውስተ መካነ ምኵናን ወአዘዘ ያብጽሕዎ ነቤሁ ለቅዱስ ቶማስ ወነሥአ አልባሲሁ ወአቅነትዎ ወአቀምዎ ቅድመ ገጹ ለንጉሥ። ወይቤሎ ንጉሥ አንተ አግዓዚኑ አው ገብር። ወይቤሎ ቅዱስ ቶማስ አነ ገብሩ ለእግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኢኮነ ለከ ሥልጣን ላዕሌሁ።

፲. ወይቤሎ ንጉሥ ለምንት ጐየይከ እምብሔርከ ወመጻእከ ኀበ ዝንቱ መካን። ወይቤሎ ቅዱስ ቶማስ መጻእኩ ኀበ ዝንቱ መካን አግብእ ዘንተ ሕዝበ እምስሕተት። ወአነሂ እፈልስ እምዝንቱ

የት ነው? አለው። ቅዱስ ቶማስም አምላኬ የሰማይና የምድር አምላክ ነው። ሰውር ሰሙንም ልትሰማ አይገባህም። ግልጥ ሰሙ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው አለው።

11. ንጉሡም እኔ ላጠፋህ አልሻም አንተን ያገለገልኸህ እንጂ። አንተ ግን ከፉ ማድረግን አወቃህ። በዚህች ሀገርም ጥንቁልናህን ግልጥ አደረግህ፣ በሕንደኬ የሚኖሩ ሁሉ ሰምተዋልና። ነገር ግን ጥንቁልናህ ሁሉም ይሻር ዘንድ አገድልሃለሁ፣ በየሀገሩ ያሉትን ሰምህንም ጥንቁልናህንም ይረሳሉ አለው። ቅዱስ ቶማስም ከዚህ ዓለም ከተለየሁ በኋላ ሥራዬ የጸና ይሆናል አለው። ንጉሡ መስቴምስም እንዴት እንግደለው አለ። እርሱ ከሚከቡት ሕዝቦች የተነሣ ይፈራ ነበርና። ከመካንንቱ ከሀገሩ ሽማግሌዎች ብዙዎቹ በቅዱስ ቶማስ ስብከት አምነዋልና።

12. ተነሣና ቅዱስ ቶማስን ያዘው። ከሀገርም ወጡ። ከእርሱ ጋርም የጦር መሣሪያ የያዙ ብዙ ሠራዊት ነበሩ። ከሕዝቡ የቀሩትም እርስ በእርሳቸው ንጉሡ ከእርሱ ጋር ሊጫወት ይሻል ይሉ ነበር። ከእርሱም ተመለሱ። ንጉሡም ከሀገሩ ሁለት ምዕራፍ ያህል በራቀ ጊዜ ከልጁ ጋር ከሠራዊቱ ዐሥራ አምስት ሰዎች ነበሩ። ከሀገሩ ሰዎችም ታላቅ ገሸር ነበር። ወደ ታላቅ ተራራ እንዲሄዱና በዚያ እንዲገድሉትም አዘዘ። ንጉሡም ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

13. ሕዝቡም በተረዱ ጊዜ ሊያድኑት ፈልገው በቅዱሱ መንገድ ተቀዳደሙ። ከእርሱ ጋር የነበሩ ሠራዊቱም ለመግደል ተፋጠኑ። ከእነርሱም ሁለቱ በቀኙ ሁለቱ በግራው ቆመ። በእጃቸውም ጦር ነበር። ሹመም እጁን በእርሱ ላይ አሳረፈ፣ የተቀደሰው ሐዋርያም ታላቅ ምስጢራዊ ጸጋን የሚያድል ነውይል ነበር። አራቱ ወንዶች የለውነቱን ምኩራብ ሊያፈርሱ ተዘጋጅተዋል።

ግለም። ወይቤሎ ንጉሥ መኑ ስመ አምላክከ ወእንተኑ እምአይቱኑ ብሔርከ። ወይቤሎ ቅዱስ ቶማስ አምላኪየ አምላክ ሰማይ ወምድር ውእቱ። ወኢይትከሃለክ ከመ ትስማዕ ስሞ ዝኦ ዳዕሙ ስመ አሠርቱ ኢየሱስ ክርስቶስ።

፲፩. ወይቤሎ ንጉሥ አነ ኢፈቀድኩ አንገሎክ፣ ወእንተ አብዛኅክ ገቢረ እክይ። ወረሰይክ ሥራየክ ከሠተ ውስተ ዛቲ ሀገር እስመ ሰምዑ ዙሎሙ እለ ይነብሩ ውስተ ብሔረ ሕንደኬ ዳዕሙ አነ እቀትለክ ከመ ይሠዓር ኵሉ ሥራይክ ወይርሥዑ ስመክ ወሥራየክ እምዙሉ በሐውርት። ወይቤሎ ቅዱስ ቶማስ እስመ ግብርየ ውእቱ ይከውን ጽኑዓ እምድኅረ ፍልሰት እምዝንቱ ዓለም። ወመስቴምስኒ ንጉሥ ይቤ እፎኑ ንቀትሎ እስመ ውእቱ ይፈርህ እምሕዝብ አለ የዓውድዎ፤ እስመ ብዙኃን እመኪንንት አምኑ ዜናሁ ለቅዱስ ቶማስ ወእምዓበይተ ሀገር ወብዙኃን በሐውርት።

፲፪. ወንጉሥኒ ተንሥአ ወነሥኦ ለቅዱስ ቶማስ ወወፅኡ እምሀገር ወምስሌሁ ብዙኃን ሠራዊት ይጸውሩ ንዋየ ሐቅል ወተርፈ እምሕዝብ ይብሉ፤ እስመ ንጉሥ ይፈቅድ ይትናገር ምስሌሁ በበይናቲሆሙ ገብኡ እምኀቤሁ። ወሶበ ርኁቀ ንጉሥ እምሀገር ዘይከውን ፪ተ ምዕራፈ ፲ቱ ወሯቱ ብእሲ እምሠራዊት ምስለ ወልዱ። ወዓቢይ መኰንን እምሰብአ ሀገር ወአዘዞሙ ከመ ይሐሩ ኀበ ደብር ነዋህ ወበህየ ይቅትልዎ። ወገብአ ንጉሥ ኀበ ሀገሩ።

፲፫. ወሶበ አእመሩ ሕዝብ ተባደሩ ውስተ ፍኖቱለቅዱስ ይኅሥሡ አድኅኖቶ። ወሠራዊትኒ እለ ኮኑ ምስሌሁ አፍጠኑ ቀቲሎቶ ወቆመ ፪ እምኔሆሙ በየማኑ ወፀቱ በፀጋሙ ውስተ እደዊሆሙ ኦያንው። ወመመኰንን አንበረ እደዊሁ ላዕሌሁ። ወኮነ ቅዱስ ሐዋርያ ይብል ምሥጢር ኅቡዕ ዘይፈጽም ጸጋ ልዕልተ አኮ ይመጥወኒ ድካመ ሥጋ። እስመ ፬ቱ ዕደው

ምድርም ከእነርሱ የተነሣ መጽኖዬ የሆነች የአራቱ ፍጥረታት አምሳል ናት አለ።

14. ከእነርሱ ጋር ወደሚገድሉበት ቦታ በደረሰ ጊዜም እንዲህ ሲል መለሰላቸው። ካገራን ስመ፣ ከዚህ ዓለም መለየቱንም ተረዳ። የልባችሁ ሓዘንም የታወረ አይሁን። ጾራችሁም የማይሰማ አይሁን፣ ያስተማርኋችሁ በልባችሁ ያድር ዘንድም በእግዚአብሔር እመኑ። ጾራችሁንም ክፉቱ የሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ በንጽሕና ትሁን። ይህችም ወደ እግዚአብሔር የምታቀርባችሁ ሕይወት ናት።

15. ቅዱስ ቶማስም የንጉሡን ልጅ መያቀው ስያኖስን አለው። አንተ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋዩ ነህ። ወደ አምላኬ እንድጸልይ ይተውኝ ዘንድ ለእነዚህ አገልጋዮች ዋጋቸውን ስጥ ይህን ያደርግ ዘንድ እርሱ አገዛኋቸዋልና። የተባረከው ሐዋርያም እጆቹን ዘረጋ። እግዚአብሔር አምላኬ ተስፋዬ፣ መረጋጊያዬ፣ መድኃኒቴ ነህ፣ ያጸናኸኝ፣ ለአንተ እንድገዛ ልቡናዬን ዝግጁ ያደረግህም አንተ ነህ። በጎልማሳነቴ ወቅት ትዕግሥትን የሰጠኸኝ አንተ ነህ። የሕይወት ቦታ ሆንህልኝ። ከጉስቁልና ከጥፋትም አዳንኸኝ፤ ጠበቅኸኝም እያለ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።

16. ሰውነቴ በሴቶች እንዳይጐላቆል ዕውቀትን የሰጠኸኝ አንተ ነህ። ምኩራቤን ለአንተ የተቀደሰ አድርጌ ጠበቅሁ። አፌም አንደበቴም ምስጋናህን ተናገሩ። ለእኔም ምሕረትህ የበዛ ነው ሀብትን አልፈለግም። አንተ ለሚሹት ይህ ዓለም ከንቱ ነው ብለሃልና። እኔም በዓለም ስኖር ድህነትን ወደድሁ። ወደ አንተ እንድሆን አዘጋጅተህልኛልና። ዘለዓለማዊውን መንግሥትም ከፍተህልኛልና። በአንተ ለሚያምኑትም ሁሉ ከፍተሃልና።

17. ውድህን ትእዛዝህንም ፈጸምሁ። ግርፋቱ ሁሉ በእኔ ላይ በዛ። ድካምንም ታገሥኋት። ይህ ሁሉ ስለስምህ በመሆኑ በእኔ ዘንድ ጣፋጭ ነበር። አንተ ተስፋዬ ነህና ሰውነቱም በአንተ ታመነች። ድካሜም በከንቱ አይሁን ልቦናዬን

ድልዋን ይንሥቱ ምኩራብ ሥጋየ እስመ ምድር አምላለ ፀቱ ፍጥረት እለ ጽንእየ እምኔሆሙ።

18. ወሰበ በጽሐ እምኔሆሙ ነበ መካን ዘይቀትልዎ ቦቱ አውሥአሙ እንዘ ይብል ስምዑ ነገርየ ወፀአትየ እምዝንቱ ወኢይኩን ልብክሙ ዕውረ። ወኢትኩን ዕዝንክሙ ጽሙመ። ወእመኑ በእግዚአብሔር ዘዜነወክሙ ቦቱ ክመ ይባእ ነገርየ ውስተ ልብክሙ ወአዕሳኒክሙ አርህው፤ ወትኩን ሀሎ መዋዕለ ሕይወትክሙ በንጽሕና እንተ ይእቲ ሕይወት ዘታቀርበክሙ ነበ እግዚአብሔር።

19. ወቅዱስ ቶማስኒ ይቤሎ ለመይቀውስያኖስ ወልዱ ለንጉሥ እስመ አንተ ላዕኩ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሀብ ለእሎንቱ ገባርያን ዕሤዮሙ ክመ ይጎድጉኒ እጸሊ ነበ አምላኪየ፡ ወውእቱ አዘዘሙ ክመ ይግበሩ ዘንተ፤ ወሐዋርያኒ ቡሩክ ሰፍሐ እደዊሁ ወአስተብቍዓ እግዚአብሔርሃ እንዘ ይብል እግዚአብሔር አምላኪየ ተስፋየ መናዝገየ ወመድኃንየ ዘአጽናዕከኒ ወረሰይከኒ ልብየ ድልወ ለኵነኔከ አንተ ዘወሀብከ ሊተ ትዕግሥተ እምውርዙትየ። ወኮንከ ሊተ መካነ ሕይወት ወዓቀብከኒ እምርስሐት ወእሙስና።

20. አንተ ውእቱ ዘወሀብከኒ አእምሮ ክመ ኢይርሳሕ ሥጋየ በአንስት። ወዓቀብኩ ምኵራብየ ቅዱሰ ለከ አፋየ ወልሳንየ አይድዓት ስብሐቲከ ላዕሌየ፤ ብዙኅ ምሕረትከ ሊተ ወኢፈቀድኩ ብዕለ፤ እስመ አንተ ትቤ ዝንቱ ዓለም ኵሉ ከንቱ ውእቱ ለእለ ይፈቅድዎ። ወአንሰ ፈቀድኩ በውስተ ዓለም ንዴተ፤ እስመ አስተዳለውከኒ ነቤከ ወአርኃውከ ሊተ መንግሥተከ ዘለዓለም ወኵሉመ እለ የአምኑ ብከ።

21. ፈጸምኩ ፈቃደከ ወትእዛዘከ። ወበገዞን ላዕሌየ ኵሉ መቅሠፍታት ወተዓገሥክዋ ለድካም። ወኮነ ዝንቱ ኵሉ ጥዕም በነቤየ በእንተ ስምከ ተወከለት ነፍስየ ወኢይኩን ፃማየ በከንቱ

ተቀብል ከራትህ አትጣለኝ። በልቡናዬ የዘራሃውን የተከበሩ ትርንጫፎችም ጠላት አያንቀላቸው። የሰጠኸኝን ገንዘብም ወደ ማረፊያ መለስሁ፤ የመጣህ ቦታውም ዐሥር ነው።

18. ይህን ዓለም ተውሁ፤ አንተንም ተከተልሁ። እርዳኝ አድነኝም ወደ ማዳንህ ተመለከትሁ፤ ያዘገየኸኝን ትእዛዝህንም ፈጸምሁ። እንደ ማፈራ ጽኑ አገልጋይም ስምህን አደረስሁት። በበጉው ነገር ሁሉ ወገቤን ታጠቅሁ። መረገጫየንም በወንጌል በሰላም መንገድ አሰሩህ። በራምቼን ጠመድሁ ሞፈሮቹንም ያዝሁ። እርሻዎንም አረስሁ ትልሜ እንዳይበላሽም ወደ ኃላዬ አልተመለስሁም ምድርም አበቀለች። የመከሩ ጊዜም ደረሰ ዋጋዬን እንደተቀበልሁ ድካሜን እፈጽማለሁ፤ ወደዕረፍትም ያደርሰኛል።

19. መጀመሪያም ሁለተኛም ሦስተኛም ፊትህን አይ ዘንድ ጊዜየን ጠበቅሁ፤ ለክብርህም እሰግዳለሁ። ከበጐ ነገር እጠግብ ዘንድም ክፉ ነገርን ጣልኋት ፈቃድህንም ሁሉ ፈጸምሁ። ወደኋላየም ተውሁት፤ የክብርህን አክሊል ሰማያዊ ውን ዋጋ እቀበል ዘንድ ለሌላው ዕንቅፋት እንዳ ልሆን ቀደምሁ። ዕባብም /ሰይጣንም/ በመንገዴ አይቁም። የዕፉኝት ልጅም በእኔ ላይ አይነሣ ከእኔ ይራቁ እንጂ የጨለማ አበጋዞች ሁሉ በእኔ ዘንድ አይቁሙ። ለአንተ፤ ለአብና አዳኝ ለሆነ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን።

20. ብፁዕ ቶማስም ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ ፊቱን ወደ ወታደሮቹ አዞረ። የንጉሣችሁን ፈቃድ ፈጽሙ አላቸው። ከሠራዊቱ አራቱ መጡና በጦር ወጉት። ስለዚህም ከመሬት ወደቀ። ነፍሱንም ሰጠ። ወንድሞችም በዚያ የነበሩትም አለቀሱለት። የሚያምሩ ልብሶችንም አመጡና ገነዙት፤ በቀደሙ ነገሥታት መቃብርም አስቀመጡት። ስቁሬና አውስያኖስም ወደ ሀገር አልገቡም። እነርሱም በዚች ዕለት በመቃብሩ ተቀመጡ።

መተማው ስእለትየ አትማድፈኒ እምትድመ ገጽከ አፅቡቀ ክቡረ ዘዘራእከ ውስተ ልብየ ኢርምልሖሙ ጸላኒ ምናኒተ ዘወሀብከኒ አግባእከ ዝአለ ይትፈድፈድ መክነ ረባት ዓሠርተ።

፲፮. ወንድየ ዘንተ ዓለመ ወተለወከከ ርድአኒ ወእድነንኒ ነጸርከ ነበ አድኅኖትከ ወፈጸምከ ትእዛዘከ ዘአዘገዘከኒ ባቲ አብጸሕክም በከመ ገብር ጽኑዕ ይፈርሆ ለስምከ ቀንትከ ሐቌየ ወሰተ ዙሉ ሠናይ ወእርኃብከ መከየድየ ወሰተ ፍኖተ መንገል ወለላም ወጸመድከ አባዕርየ ወአኃገዘከ መዋፍርትየ፤ ወሐረስከ ገራህትየ ወኢነጸርከ ድሂየ ከመ ኢይጽንን ትልምየ ወአብቁለት ምድር። ወበጽሐ ጊዜ ማዕረር ወከመ ነሣእከ ዕሤተ ወፈጸምከ ድካመ ወአብጽሐኒ ወሰተ ዕረፍት።

፲፱. ወዓቀብከ ቀዳሚ መዋዕልየ ዳግምየ ውኅልየ ከመ እርአይ ገጸከ፤ ወእሰግድ ለስብሐቲከ ገደፍከዋ ለእኪት ከመ እጽገብ እምሠናያት። ወፈጸምከ ዙሎ ፈቃደከ ወአግባዕከ ድኅሬየ ዳዕሙ ቀደምከ ከመ ኢይኩን ዕቅፍተ ለባእድ ከመ እንሣእ አክሊለ ስብሐቲከ ወዕሤተ ሰማያዊ። ወኢይቁም ለከይሲ ውስተ ፍኖትየ ወኢይቁም ላዕሌየ ውሉደ አፍዖት ወኢይቅረቡ ኀቤየ ኃይለ ጸልመት ዳዕሙ ይርኃቁ እምኔየ፤ እስመ ለከ ስብሐት ወለአቡከ ቅዱስ ወመንፈስ ቅዱስ ማኅየዊ ለዓለመ ዓለም አሜን።

፳. ወሶበ ፈጸመ ብፁዕ ቶማስ ጸሎቶ ሜጠ ገጸ ኀበ ሐራ ሰገራት ወይቤሎሙ ፈጽሙ ፈቃደ ለንጉሣክመ። ወበጽሑ ፬ እምሠራዊት ወረገዝዎ በሥናት። ወበእንተዝ ወድቀ ዲበ ምድር ወመጠወ መንፈሶ ወአኃውኒ ወእለ ይነብሩ በከዩ ላዕሌሁ። ወአምጽኡ ሠናያተ ንጹሐተ አልባሳተ ወገነዝዎ ወአንበርዎ ውስተ መቃብረ ነገሥት ቀደምት። ወስቁሬ ወአውሥያኖስ ኢቦኡ ሀገረ። ወውእቶሙኒ ነበሩ ውስተ መቃብር በይእቲ ዕለት።

፳፩. ወአስተርአየ ሎሙ ቅዱስ ቶማስ ወይቤሎሙ ናሁ አነ ይእዜ ሕያው ለምንት አንትሙ ንቡራን ተዓቅቡኒ ናሁ ተመለወኒ አንትሙ ንቡራን ተዓቅቡኒ ናሁ ተመለወኒ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥየ። ወናሁ ነግእኩ ሀበተ ዘአሴፈዋ ቢኃይለእግዚአብሔር ወይእዜኒ ተንሥኡ እምዝንቱ መካን ወአእምሩ ከመ አንትሙ እምድኅረዝ መዋዕል ትወፅኡ እምዝንቱ ዓለም ኢትትሀከዩ በእንተ አድኅኖ ነፍሳቲክሙ። ወአንትሙሰ ትገብኡ ኀቤየ።

፳፪. ወምስትዮስኒ ንጉሥ ወዚርያስ ነሥኡ አንስትያሆሙ ጥርባንያ ወአጥባና ወቀሠፍዎን ዓቢየ መቅሠፍተ ለእመ ይፈቅዱ ወይኅድጉ እምኔሆሙ ንጽሕና ወይግብኡ ኀበ ምስካቢሆሙ ወዓበዩ። ወበእንተ ዝንቱ ቅዱስ ቶማስ ተከሥተ፤ ወይቤሎሙ ኢትርስዑ ነገርየ ዘነገርኩክሙ። እስመ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ይረድአክሙ።

፳፫. ወምስትዮስኒ ወዚርያስ ሶበ አእመሩ ከመ አንስትያሆሙ አበያ ፈቃዶን እምአምታቲሆን ኀደግዎን ከመ ይኩና በከመ ፈቀዱ። ወአስተ ጋብኡ ኵሎ አኃወ ይትመሀሩ በበይናቲሆሙ ትእዛዘ እግዚአብሔር እንዘ ይትፌሥሑ በሀበተ እግዚአብሔር ወበጸጋ መንፈስ ቅዱስ።

፳፬. ወለአስትዮስኒ ወልደ ወልዱ ለንጉሥ አኃዞ ጋኔን ሀለየ ንጉሥ ወይቤ ምንተኑ ዘእገብር ዘንተ በእንተ ዘአለውክዎ ለሐዋርያ ወኢተመጠውኩ ነገሮ። ወውእቱ በጽሐ ኀበ መቃብሩ ለቅዱስ ቶማስ ከመ ይንሣእ እመግነዙ ቀረጸ ከመ ይሣለቅ ውስተ ክሣደ ወልዱ። ወውእቱ ይብል አነ አአምን እስመ እግዚአብሔር ይፈውሶ ለወልድየ።

፳፭. ወበእንተዝ አስተርአየ ሎቱ ቅዱስ ቶማስ ወይቤሎ መስትያኖስ ኢአመንከ ወአነ ውስተ ሕይወት ወተአምን ብየ እምድኅረ ሞትኩ ዳዕሙ ኢትፍራህ እግዚአብሔር ይሣሃል ላዕሌከ እስመ ውእቱ ይክልእ ጸጋሁ። ወሶበ አርኃወ

21. ቅዱስ ቶማስም ተገለጠላቸው። እኒ ዛሬ ሕያው ነኝ እናንተ ተቀምጣችሁ ለምን ትጠብቁኛላችሁ። እነሆ ንጉሤ ኢየሱስ ክርስቶስ እነሆም በእግዚአብሔር ፈቃድ ተስፋ የማደርጋትን ሀብት ሁሉ ተቀብያለሁ። ዛሬም ከዚህ ቦታ ተነሡ እናንተም ከዚህ ዘመን በኋላ ከዚህ ዓለም እንደምትለዩ ዕውቱ ነፍሳችሁን ለማዳንም አትስነፉ። እናንተ ወደ እኒ ትመጣላችሁ አላቸው።

22. ንጉሥ ምስትዮስና ዚርያስም ሚስቶቻቸውን ጥርባንያንና አጥባናን ይዘው ጽኑ ግርፋትን ገረፏቸው። ከወደዱ ከእነርሱ በንጽሕና መኖርን እንዲተው፤ ወደመኻታቸው እንዲመለሱ ነገሯቸው እነርሱ ግን እንቢ አሉ። ስለዚህ ቅዱስ ቶማስ ተገለጠና የነገርኋችሁን ነገሬን አትዘንጉ፤ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ይረዳችኋልና አላቸው።

23. ምስትዮስና ዚርያስም ሚስቶቻቸው እንቢ እንዳሏቸው በተረዱ ጊዜ እንደፈለጉ ይሆኑ ዘንድ ተዋቸው። በእግዚአብሔር ሀብት በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እየተደሰቱ እርስ በእርሳቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲማሩም ወንድሞችን ሁሉ ሰበሰቡ።

24. የንጉሡን የልጅ ልጅ አስተዮስንም ጋኔን አደረበት ንጉሡም አሰበ። የማደርገው ምንድን ነው? ሐዋርያውን ወንጀለኛ ስላደረግሁት፣ ትምህርቱንም ስላልተቀበልሁት ነው አለ። እርሱም በልጁ አንገት አድርጐ ለመዘባበት ከመግነዙ ቁራጭ ይወስድ ዘንድ ወደ ቅዱስ ቶማስ መቃብር ሄደ። እርሱም እግዚአብሔር ልጄን ቢፈውሰው አምናለሁ አለ።

25. ስለዚህም ቅዱስ ቶማስ ተገለጠለትና መስትያኖስ ሆይ አላመንህም፤ እኔ ሕያው ነኝ ከሞትሁ በኋላ ታምንብኛለህ። እግዚአብሔር ይቅር ይልሃልና አትፍራ። እርሱ ጸጋውን ይከለክላልና መቃብሩን በከፈተው ጊዜም ከተቀ

መምህረ ኢነሥአ እምኬሃ ወኢምንተኒ እምሥጋሁ ቅዱስ እስመ ውእቱ ቦአ ውስተ ደሴት።።

፳፮. ወነሥአ መራተ መካን ዘኮነ ቦቱ ቅዱስ ወአሠረ ውስተ ክሣዱ ወይቤ አነ አአምን እስመ በጸሎቱ ለቅዱስ ይወፅእ ዝንቱ መንፈስ ርኩስ እምወልድየ፤ ወበይእቲ ሰዓት ወፅአ ሰይጣን እምወልዱ ወአምነ ንጉሥ ወሰገደ ለወንጌሎስ ቅሲስ። ወሰዓለ ውእቱ ኀበ እግዚአብሔር ወይቤሎ ቀሲስ ለእጉሁ ጸልዩ ላዕለ ንጉሥክመ ይትወከፍ እግዚአብሔር ወይኅድግ ሎቱ ኵሎ ኃጢአቶ።።

፳፯. ወገብሩ ዘንተ በትፍሥሕት ወበኃሤት በእንተ ዘርእዩ እምነቶ ለንጉሥ በእግዚአብሔር መፍቀሬ ሰብእ ንጉሠ ነገሥት ወእግዚአ አጋዕዝት ወሀቦ ለመስቲያስ ንጉሥ እምነተ ርትዕተ፤ ወተስፋ ሠናየ ወጽንዕተ። ወተዜነወ እምነቱ ወሠናያቲሁ ውስተ ኵሉ ብሔር ወያከብሮሙ ለኵሎሙ አኃው። ወይባርኮሙ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።።

፳፰. ወኮነ ይረግዝዎ ለቅዱስ ቶማስ አርባዕቱ ሠራዊቱ በ፬ ኵናት ወፈጸመ ገድሎ ላዕለ ፍኖተ ሀገረ ሕንደኬ አመ ፳ወ፮ ለወርኃ ግንቦት። ስብሐት ለአብ፤ ስብሐት ለወልድ፤ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ፤ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ወአሜን።። ጸሎቱ ወበረከቱ ለቅዱስ ቶማስ ወምሕረቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ የሃሉ ምስለ ፍቁሩ ወምስለ ኵልነ ውሉደ ጥምቀት ለዓለመ ዓለም አሜን።።

ደሰች ሥጋው ከዚያች ምንም አልወሰደም። እርሱ ወደቤቱ ገብቷልና።።

26. ቅዱሱ ከነበረበት ቦታም ዐፈር ወሰደ። በእንጉቱም አሰረው እኔ አምናለሁ በቅዱሱ ጸሎት ይህ ርኩስ መንፈስ ከልጄ ይወጣል አለ። በዚያችን ሰዓትም ሰይጣን ከልጁ ተወገደ። ንጉሡም አመነ። ለቱሱ ለወንጌሎስ ቆሮስም ሰገደ። እርሱም ወደ እግዚአብሔር ለመነ። ቱሱም ወንድሙን እግዚአብሔርን ይቀበለው ዘንድ ኃጢአቱንም ይቅር ይለው ዘንድ ስለ ንጉሣችሁ ጸልዩ አለው።።

27. ሰውን በሚወድ በነገሥታት ንጉሥ በጌቶች ጌታ በእግዚአብሔር ለንጉሡ ያለውን እምነት በተመለከቱ ጊዜ በፍጹም ደስታ ይህን አደረጉ። ለንጉሡ ለመስትያስ የቀናች ሃይማኖትንና የጸናችና መልካም ተስፋን ሰጠው። ሃይማኖቱ ደግነቱ ሁሉ በየሀገሩ ተነገረ። ወንድሞቹን ሁሉ ያከብራቸው ነበር። አብ ወልድንና መንፈስ ቅዱስንም ያመሰግናቸው ነበር።።

28. አራቱ ሠራዊትም ቅዱስ ቶማስን በአራት ጦር ወጉት። ግንቦት ሃያ ስድስት ቀን በሕንደኬ መንገድ ተጋድሎውን ፈጸመ። ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን። የቅዱስ ቶማስ ጸሎቱና በረከቱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረቱ ከወዳጁ ከ_____ጋር፤ ከሁላችን ከጥምቀት ልጆች ጋር ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን።።

ወጽሐፈ ሰንሐሳር



መለቱል መልዕልተ ዙሉ ንገር
ያድጎነነ እምዐር
(ት/ያሬድ)

ከሁሉ በላይ የሆነ መለቱል
ከጠላት ያድነናል
(ት/ያሬድ)

በማዕዝና በአማርኛ

ከመስከረም እስከ የካቲት

አርኬ

ሰላም፡ለቂርቆስ፡ለንቢረ፡ገዳም፡ዘአፍቀራ።እንዘ፡ይሰቲ፡ሐሊበ፡ቍራ።ድኅረ፡አመከሮ፡ሰይጣን፡በዘዚአሁ፡መከራ።አዕይንቲሆሙ፡ለኤልሰቆልሳት፡ነጸራ።በጊዜ፡ዕረፍቱ፡ዘኮነ፡ወቢየ፡ነከራ።

መኰንኑ ፡ ወደ ፡ አለበት ፡ አገርም ፡ ደርሰው ፡ የነብር ፡ ባለቤት ፡ በሆነ ፡ በጌታችን ፡ ኢሱስ ክርስቶስ ፡ ያመኑ ። እርሱም ፡ መኰንኑ ፡ አሠቃያቸው ፡ ኤጲስቆጶሳትም ፡ እንደሆኑ ፡ አውቆ ፡ ሥቃያቸውን ፡ አበዛ ፡ እሊህ ፡ አባቶች ፡ ግን ፡ በታላቅ ፡ ትዕግሥት ፡ የጸኑ ፡ ናቸው ። ክብር ፡ ይግባውና ጌታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ያጸናቸ ዋልና ።

፯፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መኰንኑ ፡ራሶቻቸውን ፡በሰ ይፍ ፡ያቆረቧቸው ፡ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ የሕይወት ፡ አክሊልንም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ተቀ በሉ ።

፯፡ የትዱስ ፡ ቢሶራ ፡ ሥጋው ፡ ግን ፡ ንሲል ፡ በሚ ባል ፡ አገር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይኖራል ።

፰ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቶቹው ፡ ይማረን ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

ወበጽሑ ፡ ኀቡረ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ መኰንን ፡ ወተ አመኑ ፡ በእግዚእ ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ብብሐት ፡ ውእቱኒ ፡ መኰንን ። ኮነኖሙ ፡ ወአ እሚሮ ፡ ነመ ፡ እመንቱ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ አፈ ድፈደ ፡ ነሶንኤሙ ወእመንቱሰ ። አበው ፡ ጽኑ ዓን ፡ በትዕግሥት ፡ ዐቢይ ። እስመ ፡ እግዚኦ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ያጸንዖሙ ።

፫፡ ወእምድኅረዝ ፡ አዘዘ ፡ መኰንን ፡ ይምትሩ ፡ አር እስቲሆሙ ፡ በሰይፍ ፡ ወነሥኡ ፡ አክሊለ ፡ ሕይወት ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ።

፮፡ ወሥጋሁሰ ፡ ለቅዱስ ፡ ቢሶራ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ይነብር ፡ በሀገረ ፡ ንሲል ፡

፯፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይምሐረነ ፡ በጸሎቶሙ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለም ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

አርነቴ

ሰላም ለቢሶራ ፡ ዓቃቢ ፡ መርዔቱ ፡ ለልዑል ። ኤጲስቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ መጺል ። ወሰላም ፡ ካዕበ ፡ ለእሊአሁ ፡ መድበል ። ቢስኮሰ ፡ ወፊናቢክስ ፡ ወቴዎድሮስ ፡ ኃያል ። ዘተሰንዓዉ ፡ ኀቡረ ፡ በገድል ።

፰፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ከቅዱስ ፡ ፋሲለደስ ፡ ጋር ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ሺህ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ወንዶች ፡ ሰባት ፡ ሴቶችም ፡ በሰማያትነት ፡ አረፉ ። በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

፱፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ በሮም ፡ አገር ፡ ፍሩምያ ፡ በምትባል ፡ ከተማ ፡ ለሆነው ፡ ተአምር ፡ መታሰቢያ ፡ ሆነ ።

፲፡ ይህም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ የሰማይ ፡ ሠራዊት ፡ አለቃ ፡ በሆነ ፡ በነበበረ ፡ መልአክ ፡ በሚካኤል ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በሚታዩ ፡ ድን ቆችና ፡ ተአምራቶች ፡ ምክንያት ፡ ዮናናውያን ፡ ሰዎች ፡ ሰይጣናዊ ፡ ቅናትን ፡ እንደ ፡ ቀኑ ፡ ከመ ቅናታቸውም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ በዚያ ፡ አካባቢ ፡ የሚወርደውን ፡ የወንዝ ፡ ውኃ ፡ በዚያች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ሊመል ሱትና ፡ ከሚጠብቃት ፡ መጋቢዋ ፡ ጋር ፡ በውኃ ፡ ስጥመት ፡ ሊአጠፉአት ፡ ፈልገው ፡ መለሱት ።

፲፩፡ የሰማያውያን ፡ ሠራዊት ፡ አለቃ ቅዱስ ፡ ሚካኤልም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ መጋቢ ፡ ለናር

ወወሰተ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ዮናናውያን ፡ ቀንኡ ፡ በቅንአተ ፡ ሰይጣን ፡ በእንተ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ዘያስተርእዩ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለመልአክ ፡ ክቡር ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ ሠራዊተ ፡ ሰማያት ። ወእምብዝኀ ፡ ቅንአቶሙ ፡ ፈቀዱ ፡ ከመ ፡ ይማጡ ፡ ፈለገ ፡ ማይ ፡ ዘይውኅዝ ፡ በህየ ፡ ላዕለ ፡ ይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወያጥፍእዋ ፡ በሥጥመተ ፡ ማይ ፡ ምስለ ፡ መጋቢሃ ፡ ዘየዐቅባ ።

፲፪፡ ወአስተርአዮ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ ኃይላት ፡ ሰማያውያን ፡ ለናርጢኖስ ፡ መጋቤ ፡ ቤተ ፡ ክርስ

ጢኖስ ፡ ተገለጠለት ፡ ወደርሱም ፡ ቀርቦ፡ ጸና፡አትኩራ፡አለው፡ይህንን፡ብሎ፡በእጁ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡ በትር ፡ አለቱን ፡ መታው፡ አለ ቱም ፡ ተሰንጥቆ ፡ እንደ ፡ በር ፡ ሆነ ፡ የዚያ ፡ ወንዝ፡ውኃም፡በውስጡ፡አልፎ፡ሔደ።

፲፱፡ ይህንንም ፡ ያዩ ፡ ምስጉን ፡ ልጠቢአዊሐርጎ ፡ አመሰገኑት ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልንም፡ አነበሩት።

፳፡ ከዚያች ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የወንዙን ፡ ውኃ፡ በዚያች በተሠነጠቀች ፡ አለት ፡ ውስጥ አልፎ፡ሲሔድ ፡ያዩታል ፡ወደ መላእክት፡ አለቃ ፡ሚካኤል ፡ቤተክርስቲያን ፡ከቶ ፡አይ ቀርብም።

፳፩፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምሥጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አማላጅነት ፡ ይማረን ፡ለዘላለሙ ፡አሜን።

ጢኖስ ፡ ወቀርበ ፡ ኀበዉ ፡ ወይቤሎ ፡ ጽናዕ ፡ ወኢትፍራህ ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ዘበጠ ፡ ለኰኵሖ ፡ በበትረ ፡ እደዉ ፡ ወተሠጥቀ ፡ ኰኵሖ ፡ ወኮነ ፡ ነሙ ፡ ኖኀት ፡ ወኀለፈ ፡ በውስቴቱ፡ውእቱ፡ማየ፡ፈለግ።

፲፪፡ ወእለ ፡ ርእዩ ፡ዘንተ ፡ ሰብሕዎ ፡ ለእግዚአ ብሔር፡ ስቡሕ ፡ ወአክበርዎ ፡ ለሚካኤል ፡ ክቡር፡ሊቀ፡መልእክት።

፲፫፡ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ይሬ እይዎ፡ለውእቱ፡ፈለግ፡እንዘ፡ይውኀዝ፡ወየ ኀልፍ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ኰኵሖ ፡ ወኢይ ቀርብ ፡ ኀጕራ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ፡ ሰሊቀ፡መላእክት፡ሚካኤል።

፲፬፡ ወሰብሑት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረን ፡ በትንብልናሁ ፡ ለሚክኤል ፡ ክቡር፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ጢኖስ ፡ ተገለጠለት ፡ ወደርሱም ፡ ቀርበ፡ ጸና፡አትኩራ፡አለው፡ይህንን፡ብሎ፡በእጁ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡ በትር ፡ አለቱን ፡ መታው፡ አለ ቱም ፡ ተሰንጥቆ ፡ እንደ ፡ በር ፡ ሆነ ፡ የዚያ ፡ ወንዝ፡ውኃም፡በውስጡ፡አልፎ፡ሔደ።

፲፱፡ ይህንንም ፡ ያዩ ፡ ምስጉን ፡ ልጠቢአዊሐርጎ ፡ አመሰገኑት ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤልንም፡ አነበሩት።

፳፡ ከዚያች ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የወንዙን ፡ ውኃ፡ በዚያች በተሠነጠቀች ፡ አለት ፡ ውስጥ አልፎ፡ሲሔድ ፡ያዩታል ፡ወደ መላእክት፡ አለቃ ፡ሚካኤል ፡ቤተክርስቲያን ፡ከቶ ፡አይ ቀርብም።

፳፩፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምሥጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አማላጅነት ፡ ይማረን ፡ለዘላለሙ ፡አሜን።

፳፪፡ ወእምይእቲ ፡ ዕለት ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ይሬ እይዎ፡ለውእቱ፡ፈለግ፡እንዘ፡ይውኀዝ፡ወየ ኀልፍ ፡ ውስተ ፡ ይእቲ ፡ ኰኵሖ ፡ ወኢይ ቀርብ ፡ ኀጕራ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ፡ ሰሊቀ፡መላእክት፡ሚካኤል።

፳፫፡ ወሰብሑት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረን ፡ በትንብልናሁ ፡ ለሚክኤል ፡ ክቡር፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ኦርቤ

ኀላም ፡ እብል ፡ ለዓቢይ ፡ መንክሩ ። ዘተከሥተ ፡ ዮም ፡ በውስተ ፡ ዳቤሩ ። ፈለገ ፡ ማይ ፡ ይሚጡ ፡ እንዘ ፡ ይመክሩ ። ተሠጥቀ ፡ ኰኵሖ ፡ እንተ ፡ ዐላውያን ፡ አንበሩ ። ሶበ ፡ ሚካኤል ፡ ዘበጠ ፡ በበትሩ ።

፲፬፡ ወሰብሑት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረን ፡ በትንብልናሁ ፡ ለሚክኤል ፡ ክቡር፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ኦርኬ

ናሁ ፡ ይሬኢ ፡ እምነ ፡ መንግሥቱ ፡ ዘተድህለ ። መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያድምዕ ፡ ወዘኢ የኀልፍ፡ ብዕለ ። ውስተ ፡ ጕንደ ፡ ዕፅ ፡ ይቡስ ፡ አመ ፡ ተለዓለ ። በትሩፋቲሁ ፡ ከመ ፡ ያርኢ ፡ ኃይለ ። አሥረዐ ፡ ሶቢሃ ፡ ወአውጽአ ፡ ቈጽለ ።

ኦርኬ

ናሁ ፡ እምነ ፡ መንግሥቱ ፡ ዘተድህለ ። መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያድምዕ ፡ ወዘኢ የኀልፍ፡ ብዕለ ። ውስተ ፡ ጕንደ ፡ ዕፅ ፡ ይቡስ ፡ አመ ፡ ተለዓለ ። በትሩፋቲሁ ፡ ከመ ፡ ያርኢ ፡ ኃይለ ። አሥረዐ ፡ ሶቢሃ ፡ ወአውጽአ ፡ ቈጽለ ።

* * *

ዕ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሥሂሆነ ፡ በኢብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ መስከረም ፡ ዐሥር፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ጼዴንያ ፡ በምትባል ፡ አገር ፡ ሥጋ የለበሰች ፡ ከምትመስል ፡ ሥዕል ፡ ከሠሌዳዋ ፡ ቅባት ፡ እየተንጠፈጠፈ ፡ አምላክን ፡ የወለደች፡ የእመቤታችን ፡ የድንግል ፡ ማርያም ፡ ተአምር፡ ተገለጠ።

ዑ፡ ይህንም ፡ ሥዕል ፡ የሣላት ፡ ወንጌላዊ ሉቃስ፡ ነው ፡ ይባላል ። ወደ ፡ ጼዴንያ ፡ አገርም ፡ የመጣችበት ፡ ምክንያት ፡ አንዲት ፡ ስሟ ፡ ማርታ ፡ የሚባል ፡ መበለት ፡ ሴት ፡ ነበረችና ፡ ቤቷንም ፡ ለእንግዳ ፡ ማደሪያ ፡ ያደረገች ፡ ናት ፡

ዕ፡ በ፭ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሥሂሆነ ፡ በኢብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ መስከረም ፡ ዐሥር፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ጼዴንያ ፡ በምትባል ፡ አገር ፡ ሥጋ የለበሰች ፡ ከምትመስል ፡ ሥዕል ፡ ከሠሌዳዋ ፡ ቅባት ፡ እየተንጠፈጠፈ ፡ አምላክን ፡ የወለደች፡ የእመቤታችን ፡ የድንግል ፡ ማርያም ፡ ተአምር፡ ተገለጠ።

ዑ፡ ይህንም ፡ ሥዕል ፡ የሣላት ፡ ወንጌላዊ ሉቃስ፡ ነው ፡ ይባላል ። ወደ ፡ ጼዴንያ ፡ አገርም ፡ የመጣችበት ፡ ምክንያት ፡ አንዲት ፡ ስሟ ፡ ማርታ ፡ የሚባል ፡ መበለት ፡ ሴት ፡ ነበረችና ፡ ቤቷንም ፡ ለእንግዳ ፡ ማደሪያ ፡ ያደረገች ፡ ናት ፡

* * *

ዖ፡ በእሙ ፡ አኃት ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈ አምላክ ፡ አሜ ። ፲፩ ፡ ለመስከረም ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ ተከሥተ ፡ ተአምሪሃ ፡ ለእግዝእትነ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወሲቲ ፡ አምላክ ፡ በሀገረ ፡ ጼዴንያ ፡ እንዘ ፡ ያንጸፍጽፍ ፡ ቅብዕ ፡ እምሠሌዳ ፡ ሥዕል ፡ ዘልብስተ ፡ ሥጋ ፡ ትመስል ።

዗፡ ወለዛቲ ፡ ሥዕል ፡ ተብህለ ፡ ከመ ፡ ወንጌላዊ ፡ ሉቃስ ፡ ሠዓላ ፡ ወምክንያቱ ፡ ምጽአታሰ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ጼዴንያ ፡ እስመ ፡ ሀለወት ፡ አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ መበለት ፡ ዘስማ ፡ ማርታ ፡ ዘረሰየት ፡ ቤታ ፡ ማኀደረ ፡ ለአናግድ ፡ ወጥቀ ፡